


# ሞቶ መነሳት

**ተሾመ ተንኮሉ**
**(እውነተኛ ታሪክ)**
**ካፒቴን (አየር ኃይል)**



ካፒቴን ተሾመ ቶንክሉ (በስተቀኝ) በበረራ ዝግጅት ላይ

ግንቦት '98 ድንገት ከፍተኛ ግርግር ተሰማ። ትልቂቱ ኢ.ትዮጵያ ትንሺቱ ኤርትራ ወረረችኝ በማለት ወያኔዎች ያላዝናሉ።የሚገቡበት ቀዳዳ ጠፍቱአቸዋል። ምክንያቱን አልወቀው እንጂ ወያኔዎች ከፍተኛ ውጥረት ላይ ናቸው።ያገኙትንም ሁሉ እያፈሱ ወደ ትግራይ ማጉዋጉዋዝ ጀምረዋል :: 'ሁሉም ነገር ወደ ጦር ግምባር' የሚለውን የደርግ መፈክር እያስታወሰኝ ነው ::

አየር ሃይልም ከክተት አዋጁ ጀምሮ በአስቸኩይ ለውጊያ ዝግጁ እንዲሆን ትእዛዝ የደረሰው በመሆኑ እኔም ከስልጠና ስኳድሮን ወደ ተዋጊ ሚግ -23 ቦምብ ጣይ ስኳድሮን ተዛውሪያለሁ ::

ሁሉም በራሪ መኖሪያ ቤቱን ለቆ ደብረ ዘይት በሚገኘው የአየር ሃይል መኮንኖች ክበብ እንዲኖር በወጣው ትእዛዝ መሰረት ጠቅልሎ ገብቱአል።እኔም ከአዲስ አበባ መኖርያ ቤቴን ለቅቄ ደብረ ዘይት ከትሚያለሁ ::

ጠዋት የስልጠና ስኳድሮን፣ከሰአት በኋላ ደግሞ ከተዋጊ ስኳድሮን ጋር መደበኛ ተግባሬን በማከናወን ላይ ነኝ ::

በአበሻ ግንቦት 27 ቀን 1990፣በፈረንጆቹ ደግሞ ጁን 5 1998 ነው :: በጠዋቱ የስልጠና በረራዎችን አከናውኜ ከሰዓት በኋላ ደግሞ የውጊያ ስኳድሮን ሚግ -23 አውሮፕላንን የውስጥ አካል የፋሚላራይዜሽን (ትውውቅ) የክፍል ውስጥ ትምህርት እየወሰደኩኝ ነው ::

በአበሻ ከቀኑ 11 ሰዓት ይሆናል፣በፈረንጆቹ ከሰዓት በኋላ 5 ሰዓት ::

ሻለቃ በሪሁ የተባለ በአየር ሃይል የመከላከያ ሴኩሪቲ ሰራተኛ፣ለብርቱ ጉዳይ እንደሚፈልገኝ ይነግረኛል ::ትምህርት ላይ ነኝና እንደጨረስኩ እንደምንነጋገር ተስማምተን ውጪ ይጠብቀኛል ::

ሻለቃ በሪሁ ኪዳነ ማለት ከአየር ሃይሉ ዋና አዛዥ ጀነራል አበበ ተ /ሃይማኖት (የበረሃ ስሙ 'ጆቤ') ጋር በቅርብ ከሚሰሩ የትግራይ ተወላጆች መካከል አንደኛው ነው ::

ከመከላከያ ዋናው መሥሪያ ቤት ጋር የተያያዘ የደህንነት ሥራ ሲሰራ የኖረ ሲሆን፣ አየር ሃይልም ከመጣ በኋላ ያንኑ የጆሮ ጠቢነት ሥራን የሚያከናውን ነው ::

እግረመንገዱን ግን በአየር ሃይል የበረራ ት /ቤት የበረራ ሙ·ያ ሥልጠና እንዲያደርግ ተፈቅዶለት፣በመጀመርያ ደረጃ የበረራ ስኳድሮን ውስጥ ተመድቦ በችሎታ ማነስ ከበረራ ሙ·ያ የተባረረ ሲሆን፣ለወያኔዎች በሚሰጥ ልዩ ችሮታ ብቻ በሄሊኮፕተር ስኳድሮን አዛዥ ሆኖ ተመድቦ:እየሰራ:ያለ:ነው:: ::

እኔና አንድ የሥራ ባልደረባዬ የክፍል ውስጥ ትምህርታችንን ጨርሰን ስንወጣ በሪሁን ባለማግኘታችን አንዲት ለስኳድሮናችን የተመደበች መኪና እያሽከረከርኩኝ በቀድሞው ስያሜው የጀግኖች አምባ፣በወያኔዎች ዘመን ግን የመከላከያ ኢንጂነሪንግ ተብሎ ከሚጠራው ቅጥር ግቢ ለቀን ስንወጣ፣በሪሁ ከኋላ በከፍተኛ ፍጥነት እያሽከረከረ ይደርስብኝና በምልክት ካስቆመኝ በኋላ፣ወደ እኔ በመቅረብ ለከፍተኛ የሥራ ጉዳይ እንደፈሚልገኝና እርሱ በያዛት መኪና አብረን እንድንሄድ በጠየቀኝ መሰረት የያዝኳትን መኪና ከጎኔ ለነበረው የሥራ ባልደረባዬ ሰጥቼ በበሪሁ መኪና ወደ ዋናው የአየር ሃይል ግቢ አመራን ::

በመንገዳችን ላይ ግን ሱዳን ኤርትራን ደግፋ ልትወረን ጦሯን ወደ ድንበር እያስጠጋች ነውና፣ የኢትዮጵያንና ሱዳንን ወሰን የሚያካልል ለበረራ የምንጠቀምበትን ማፕ (ካርታ ) ከእኔ ቢሮ ፈልጌ እንዳገኝለት ይጠይቀኛል ::

የነገረኝ ታሪክ እውነትነት ሊኖረው እንደሚችል ባልጠራጠርም ከእኔ ቢሮ ማፕ መፈለጉ ግን አልመስልህ አለኝ ::

ይህንን ለሚያክል የአገር ጉዳይ በዚህ ላይ በሪሁን ለሚያክል ምርጥ የወያኔ ካድሬ፣ የአየር ሃይሉ የኤሪያል ፎቶ ሴክሽን (ክፍል ) በሰፊው ክፍት ሊሆን እንደሚችል ጥርጣሬ አልነበረኝም።ማፑም ከእኔ ቢሮ ይልቅ እዝያው ፎቶ ሴክሽን እንደሚሻል ግልፅ ነው ::

ይህንን በአእምሮዬ እያመላለስኩ ወደ ቢሮዬ ደረስን ::እኔ ካርታውን ስፈልግለት በሪሁ ግን ሥልክ በመደወል ተጠመደ ::እዚያ ይደውላል፣እዚህ ይደውላል ::ሻለቃ አብርሃ መንጁስን ለማግኘት:ይጥራል::

ሻለቃ አብረሃ መንጁስ ደግሞ የአየር ሃይሉ የደህንነት ክፍል ሃላፊ ሆኖ የሚሰራ ወያኔ ነው። እርግጠኛ ነኝ የትምህርት ደረጃው ኤለመንተሪን ያጋመሰ እንኳ አይደለም ::ግን ሃይለኛ ነው። ነገር ማነፍነፍ ይችልበታል፣ ከማይመቹኝ መንጋ የወያኔ ካድሬዎች ውስጥ ቁጥር አንዱ ነው ::

በሪሁ በዚህ ከሥራ ሰዓት ውጪ ቢሮዬ ድረስ ይዞኝ መጥቶ አብረሃን ለማግኘት በሥልክ መጠመዱ ግራ አጋባኝ ::እንደነገረኝ ከሆነ የፈለገኝ ለብርቱና አስቸኳይ ጉዳይ ነው፣ ታድያ ወደ ሌላ ማተኮሩ ምን የሚሉት ነው ? ለነገሩ ወያኔዎች የአገር ይሁን የግል ጉዳይ መች ያስጨንቃቸዋል ?እኔ ግን አንዴ ካርታ ፈልግልኝ ብሎኛልና ፈልጌ አምጥቼ ጠረጴዛው ላይ አስቀመጥኩለት ::በሪሁ ዞር ብሎም አላየው::

ይመስለኛል አበረሃን በሥልክ አግኝቶት ተነጋግረዋል ::ንግግራቸው በትግሪኛ በመሆኑ ሙሉ ለሙሉ አይገባኝም።እንድፈልግለት ጠይቆኝ ያገኘሁለትን ካርታ ዞር ብሎም ሳያየው እዚያው ጠረጴዛ ላይ እንደተወው እንውጣ ብሎኝ ከቢሮዬ ወጣ ስንል አብረሃ መንጁስን እዚያው እቢሮዬ ደጃፍ ላይ ግጥምጥም አልን ::

ዙርያውን ብቃኝ ማንንም ሰው ማየት አልቻልኩም፣ መኪናም በአካባቢው ዝር አላለም፡ታድያ በምን እዚህ ድረስ መጣ ብዬ ተገረምኩ። ምክንያቱም የእኔ ቢሮ የሚገኝበት የበረራ ት /ቤት ከዋናው ጠቅላይ መምሪያ የ 3 እና 4 ኪ /ሜ እርቀት ላይ ነው። ወዲያው ግን በበሪሁ መኪና ሆነን:ጉዞ:ጀመርን።

በሪሁ ያሽከረክራል፣እኔ ከጎኑ ተቀምጫለሁ፣አብረሃ ከኋላ ተሳፍሯል። በቀጥታ ሻለቃ አመዴ ወደሚባለው:ሌላው:ትግሬ:ባለሥልጣን:ቢሮ:አመራን።

አመዴ ማለት የበረሃ ሥሙ ነው።ትክክለኛ ሥሙ ግን ሲሳይ በላይ በመባል ይታወቃል። በእድሜው ገፋ ያለ፣በትምህርቱ ግን ከ 5ኛ ክፍል ያልዘለለ፣የራሱ ሃሳብ ካልሆነ በስተቀር የሌላን ሰው ሃሳብ በፍፁም በበጎ የማያይ፣ጅላ ጅል መሥሎ ግን አስቸጋሪ ሰው ነው። አቅሙን አያውቅም።

ቢተው በላይ የሚባለው የወያኔ ቁንጮ (የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦችን መንግስት ከአባተ ኪሾ ጀርባ ሆኖ ሲያስተዳድርና ሲገዛ የኖረ፣በኋላ ግን ከመለስ ጋር ተጋጭቶ በእሥር ሲማቅቅ የነበረው ) ታድያ አመዴ የዚህ ቱባ ባለሥልጣን ወንድም ነው።በዚህም ምክንያት ይመስላል አመዴ አየር ሃይል ውስጥ እንዳሻው ይፈልጣል ይቆርጣል ። ትልቁን የአየር ሀይል ኦፐሬሽን መምሪያንም ያዛል። በተጨማሪም እንደ በሪሁ ሁሉ የበረራ ሥልጠና እንዲወስድ ተፈቅዶለት በረራን ሞክሯል።ይሁን እንጂ እጅግ ደካማ በመሆኑና እድሜውም ተጨምሮ በአየር ሃይሉ ታሪክ ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅ የችሎታ ማነስ ሥልጠናውን እንዲያቆም ቢደረግም ከፍተኛ ረብሻ ፈጥሮ ከበረራ ይስቆሙትን የበረራ አስተማሪዎችን ቁም ስቅል ሲያሳይ የነበረ ነው።

ታድያ በሪሁና አብረሃ እኔን ይዘው እዚሁ የኦፐሬሽን መምሪያ ሃላፊ ነኝ ከሚለው አመዴ ቢሮ ጎራ ለማለት እኔን መኪናዋ ውስጥ እንድጠብቃቸው ነግረውኝ ወደ ውስጥ የዘለቁት።

ጊዜው እየመሸ ነው።ጠዋት ነው በማለዳ ከቤቴ የወጣሁ ነኝ … .. ደካክሞኛል።ቶሎ በጊዚያዊነት ወደ ተሰጠችኝ የአየር ሃይል መኮንኖች ክበብ መኝታ ቤቴ ቢያደርሱኝ ጓጉቼያለሁ።

በሪሁና አብርሃ አመዴ ቢሮ ቆይተው ከዚያም ወደ አየር ሃይሉ ዋና አዛዥ ጀ /ል አበበ ተ /ሃይማኖት ቢሮ ገቡ።እኔም የአካል ዝለቱ ሥለ በረታብኝ እዚያው መኪናዋ ውስጥ ወንበር ላይ እራሴን ጋለል አድርጌ እንደማንቅላፋት እያደረገኝ ነው ። ረዥሙና አድካሚው የጦርነት ወሬ የሚናፈስበት:ቀን:አድክሞኛል።

የአየር ሃይሉ ዋና አዛዥ አበበ ተ /ሃይማኖት በበረሃ ሥሙ ‘ጆቤ’ በመባል በሰፊው ይታወቃል። እብሪተኛ ነው።ደርግን በማሸነፋቸው ከፍተኛ እብጠት ካበጡት የወያኔ የጦር መሪዎች አንደኛው ነው። እሱ ያለው ነገር ሁሉ ተፈፃሚነት ያገኛል እየተባለ ይወራለታል። በዙሪያው

EthioLion.com

ያሉ ረዳቶቹ ሲሶ የመንግሥት ሥልጣን አለው ብለው ያምናሉ ። የቀድሞ የአየር ሃይል ከፍተኛ መኮንንችን፣ በራሪዎችን፣ባለሌላ ማዕረግተኞችን፣ሴት ወንዱን ሁሉ ቁጭ ብድግ ያሥደርጋል።እሱ የሚናገረው ቃል የእግዚአብሄር ቃል አይነት እንደሆነች መወሰድ ከተጀመረ ውሎ አድሯል።

እዚያችው መኪና ውስጥ ደገፍ እንዳልኩ የመኪናው በር ሲከፈት አይኔን ገለጥ አድርጌ ስመለከት በሪሁና አብረሃ ተያይዘው መተዋል፣ቀኑም መጨላለም ጀምሯል።ወደ መኝታ ቤትህ እናድርስህ ብለውኝ መኪናዋን በሪሁ ሲያንቀሳቅስ የእፎይታ ረዥም ትንፋሽ ተነፈስኩ።

ገና መንገድ እንደጀመርን አብረሃ ከኋላ ተቀምጦ ሲጋራ አቀጣጠለ።ከወያኔዎቹ ብሽቅ ባህርይ ውሥጥ ለሰው ሥሜት ደንታ ማጣታቸው ነበር።መኪና ውስጥ፣ምግብ ቤት ውስጥ የትም ቦታ ...... .. ያጨሳሉ።ለእነርሱ ሁሉም ሥፍራ ምንም የማድረግ ፈቃድ አለን ብለው ጭንቅላታቸውን:አሳምነውታል።

መኪናው ውሥጥ መጨሱ አልተመቸኝም።ከድካም ጋራ ተዳምሮ የሲጋራው ጢስ አቅለሸለሸኝ።

ድንገት እንኳ ሰምቶኝ ሲጋራውን መኪና ውስጥ ማጨሱን እንዲያቋርጥ እንዳልነግረው በረዥም የሬድዮ ግንኙነት ተጠምዷል።አብረሃ እርጋታ አይታይበትም፡ለነገሩ በተፈጥሮው ቀዥቃዣ ነው።ሰውነቱ እላዩ ላይ ያለቀ ጣዕረ ሞት።አይኖቹ ጉድጓዳቸው ውሥጥ እንኳ ሆነው ተጠራጣሪና ያለማቋዋረጥ ወዲያ ወዲህ ያማትራሉ።ምላሱ መቼም አይጣል ነው።በዚህ እየሞተ ባለ ሰውነቱ ላይ ሲጋራ! አንዴ በሬድዮ ሌላ ጊዜ ደግሞ ከበሪሁ ጋር ያወራሉ። ወሪያቸው እኔን ያገለለ የትግርኛ ቋንቋ በመሆኑ ከሲጋራው በላይ አስጨንቆኛል።ባዕድነትም፣ ብቸኝነትም ዋጠኝ።

በወሪያቸው መሃል ሲጋራውን ላስቆመው ወደ አብረሃ ዞር ስል፣ ከጨረሳት ሲጋራ ላይ አዲስ ሲጋራ ሲለኩስ ደረስኩበትና ተሥፋ ቆርጬ ያሰብኩትንም ሳልናገር ከዞርኩበት ተመልሼ ወደ ፊት ለፊቴ በመዞር ተስተካክዬ ተቀመጥኩ ።ይሁን እንጂ በዚህ ዓይነት ብዙ መጓዝ አልቻልኩም ። ሁኔታው ሁሉ እየከነከነኝ በመምጣቱ ፣ በተጨማሪም የሬድዮ ግንኙነቱ ፣ በማይገባኝ ቋንቋ መጯጯኋቸው ስለበረታብኝ ተመልሼ ወደ አብረሃ አቅጣጫ እንደገና ዞሬ ስመለከት፡እኛ ከአለንባት መኪና ውሥጥ ሆኖ ከኋላ ከሚከተለን መኪና ጋር ምልክት ሲሰጣጥና ሲነጋገር ደረስኩበት።

አንዳች ነገር ሰውነቴን ውርር አደረገኝ ። አሻግሬ ከኋላ የሚከተለንን መኪና ስመለከት ደብዛዛ ቢጫማ:ቀለም:ያለው:ቶዮታ:ላንድ:ክሩዘር:ነው።

እስከ አሁኗ ደቂቃ ድረስ የደከመ አካሌን እረፍት እንዳያደርግ ለምን ያንገላቱታል በሚል አጉል ግድየለሽነታቸው ቅር ሲለኝ አመሸሁ እንጂ አንዳች አደገኛ ነገር እየተፈፀመ መሆኑን አልተጠራጠርኩም ነበር ። እርግጥ ነው እኔን ያገለለው የትግሪኛ ቋንቋ ንግግራቸው ፣ የሬድዮ ግንኙነቱን ጨምሮ ባዕድነት እንዲሰማኝ አድርጎኛል ።ድሮም ቢሆን እኔ የእነሱ እንዳልሆንኩ ሁሉ ፣ እነሱም የእኔ ያለመሆናቸውን ስለማውቅ ባእድነቴን ተቀብዬዋለሁ።

የአብረሃ ከሚከተለን መኪና ውሥጥ ካሉ ሰዎች ጋር በምልክት መነጋገሩ ፣ በዚህ እየመሸ ባለ ሠዓት እነዚህ ሁለት ሰዎች መካከል መገኘቴ ፣ የሬድዮ ግንኙነቱ ፣ በአጠቃላይ ከእኔ ጋር አንድም የጋራ የሆነ ጨዋታ በመካከላችን ያለመነሳቱና ከሁሉም በላይ ግን ከእኔ ቢሮ ማፕ ( ካርታ ) ፈልጎ ቢሮዬ ከደረስን በኋላ ግን የማፑ ( የካርታው ) ሥም ያለመነሳቱ ፤ ሁሉንም በአንድ ጊዜ ስመዝነው አደጋ መስል ነገር ውሥጥ እሆን ያለሁት ? ከማለት ያለፈ ብዙም አልተጠራጠርኩም ።

በሰላም ሥራውን ሰርቶ የሚውልን ሰው በሠላም ወደ ማረፊያው ለመመለስ የሚከለክለው ሰው እንደማይኖር እርግጠኛ ሆንኩ ።ነገር ግን የሆነ ነገር ደስ አልልህ አለኝ።

ይህንን እያሰላሰልኩ ባለሁበት ቅጽበት ሻለቃ አብረሃ ከኋላ ወንበር ተቀምጦ እንዳለ ከደብረ ዘይት ወደ ምዕራብ አቅጣጫ 8-10 ኪ /ሜ ላይ ወጣ ብላ ወደምትገኘው ዱከም ወስዶ እራት ሊጋብዘን እንደሚፈልግ ድንገተኛ ሃሳብ ይሰንዝራል ። እኔ መቼም ከነዚህ ሰዎች ጋር እራት የሚያገባብዝም ሆነ አብሮ የሚያስመሽ ጓደኝነትም ሆነ ቅርርብ የለኝም ፤ ... .. ታድያ የምን እራት ግብዣ እንደሚያወራ አልገባህ አለኝ ። ስለዚህም እኔ እራት መብላት እንደማልፈልግና ባይሆን እኔን ወደ መኝታ ክፍሌ አድርሰውኝ እነሱ ለእራት እንዲወጡ ሃሳቤን ገለፅኩ ። ሁለቱም መልስ አልሰጡኝም ። በዚች ቅፅበት ወደ ዱከምና መኮንኖች ክበብ መገንጠያ ( በቀለ ሞላ ሆቴል ) ጋ ስንደርስ መኪናዋን እያሽከረከረ ያለው በሪሁ እራት አብሪያቸው መብላት ያለመፈለጌን ትኩረት ሳይሰጠው ወደ መኮንኖች ክበብ ከማቅናት ይልቅ ቀጥታውን የዱከምን መስመር ይዞ ፍጥነቱን ጨምሮ ተፈተለከ ። አሁን በእርግጥ ቅር ተሰኘሁ ። ሰውነቴም ተጨነቀ ። ምንድነው ነገሩ ? የሚለው ጥርጣሬዬም በረታ ።

በሪሁ ሃሳቤን ለመስረቅ ይመስላል ፍጥነቱን እየጨመረ አደገኛ አነዳድ መንዳት ጀመረል ። ወደ ኋላ ዞሬ ስመለከት ከኋላ የሚከተለን መኪና አብሮን ፍጥነቱን ጨምሮ ጭራችንን ይዞ ይከተለናል ። አብረሃ አይኑን አያርገበግብም ። ብቻ አፉን ከፍቶ በላይ በላዩ እየተነፈሰ ሲጋራውን ቶሎ ቶሎ ይስባል ። ወደ እኔ አቅጣጫ አይመለከትም ። አይኑን ከአይኔ ያሸሻል ።

በዚህ ሁኔታ ላይ እያለን የደብረ ዘይትን ከተማ እየለቀቅን ዱከም ከተማ መዳረሻ ላይ ወደ አለው ሰው አልባ ጭር ያለ ሜዳ ላይ ደረስን ። ከሁሉም በላይ አካባቢው ጨለማ ወርሶታል ። ወደ መሃል አካባቢ ስንደርስ ደግሞ አብረሃ ሌላ ጥያቄ አመጣ። መፀዳዳት እፈልጋለሁና መኪናውን አቁምልኝ ብሎ በሪሁንን ይጠይቃል። ( ይህንን ንግግር ለመጀመሪያ ጊዜ በአማርኛ ሲጠቀም ) ።

ወደ ዱከም መንደሮች ለመግባት ጥቂት በቀረችን እርቀት ላይ ሆኖ ሜዳ ላይ የመፀዳዳት ፍላጎቱ አልዋጥልህ አለኝ ። መኪናዋን እያሽከረከረ ያለው በሪሁ ግን መኪናዋን ለማቆም ፍጥነቱን እየቀነሰ ከመንገዱ ቀኝ ጠርዝ ላይ ሲያቆምና ከኋላችን ይከተለን የነበረው መኪና እኔ በተቀመጥኩበት ቀኝ ጠርዝ በኩል ሙሉ ለሙሉ እይታዬን ከልሎ ሲቆም እኩል ሆነ ። በፍጥነትም አራት ሰዎች ከቀኝ ከቆመው መኪና ውስጥ ዘለው በመውረድ እኔ በተቀመጥኩበት በኩል ያለውን በር በመክፈት በትግርኛ መጯጯህ ያለበት ትግል ቢጤ ግብግብ ከመፈጠሩ በስተቀር ብዙም ትዝ የሚለኝ ነገር የለም ።

ከሄድኩበት ሰመመን አይነት ነገር ስነቃ ፣ በመኪና ውስጥ እየተጓዝኩ መሆኔን ቀጥሎም ሰዎች በትግሪኛ ቋንቋ እንደሚያወሩ ተሰማኝ ። አካባቢዬን ለመቃኘት አይኔን ለመግለጥ ብሞክር



EthioLion.com

ምንም ለታየኝ አልቻለም ። አይኔ በአንዳች ነገር ተሸፍኗል ። እጅግ ደነገጥኩኝ ። አይኔን የሸፈነውን ነገር ለማስለቀቅ ብሞክር እጆቼን ማንቀሳቀስ ተሳነኝ ። ሁለቱም እጆቼ የፌጢኝ ታስረዋል ። ድንጋጤዬን መቆጣጠር ስለአቃተኝ ድምፅ አውጥቼ ጮህኩኝ ። የመኪናው ወለል ላይ እንዳስተኙኝና የመኪና መሸፈኛ ሸራ ነገር እንዳለበሱኝም አስተዋልኩ ።

ደጋግሜ ጮህኩ ። ዝም እንድል በማስጠንቀቂያ አይነት ቃና ተነገረኝ ። ምን እንዳጠፋሁና ወዴትስ እየወሰዱኝ እንደሆነ ደጋግሜ ጠየቅሁ ። ”ዝም ጥሩ” የሚል አማርኛ ሆኖ ትግሪኛዊ ዘዬ በያዘ አነጋገር መልስ ተሰጠኝ “ሱቅ ፅቡቅ” መሆኑ ነው በትግሪኛ ። አማራጭ አልነበረኝምና ዝም ማለትን መረጥኩ ። ያላቋረጠ የሬድዮ ግንኙነት በትግሪኛ ቋንቋ ያደርጋሉ ። አልፎ አልፎ መኪናው ሙሉ ለሙሉ ይቆማል ። ከተወሰነ ደቂቃ በኋላ ግን ያለበሱኝን ሸራ መሰል ነገር ከላዬ ይገፉና እንድነሳ ትዕዛዝ ይሰጡኛል። እጅ እግሬ በመታሰሩ ግን አልቻልኩም ። በኋላ ግን በሁለት ሰዎች ግራና ቀኝ ተደግፌ ተነሳሁ ። እንደያዙኝም ከመኪናው አወረዱኝ ። አይኔ ተሸፍኗልና ዙሪያዬን መማተር አልቻልኩም ። ግራና ቀኝ እንደተደገፍኩ መራመድ ጀመርን ። የሆነ በር ሲከፈት ይሰማኛል ::

በሩን እንዳለፍንም ደረጃ ነገር ላይ ቁልቁል ወረድን። ከዚያም በድጋሚ አንድ በር ከፍተው ወደ ውስጥ ገፈተሩኝ ። ሚዛኔን ስቼ በፊት ለፊቴ ዥሮው ብዬ ወደቅሁኝ ። ቀጥለው ግን የአይኔን መሸፈኛ ፈቱልኝ ። ወዲያው ግን በሩን ዘግተውብኝ ከውጪ ሲቆልፉት ተሰማኝ ። ዛሬ ድረስ የዚያች ክፍል በር አዘጋግ ድምፅ ጆሮዬ ላይ ያስተጋባል ። የገደል ማሚቶ ያጀበው የከባድ የብረት በር ድምፅ ......... .. ።

ዙሪያዬን ለማስተዋል ሞከርኩኝ ፤ ድቅድቅ ጨለማ ዙሪያዬን ውጦኛል ። ምናምኒት ጭላንጭል ለምልክት አትታይም ። ደንገጥሁ ፤ ጭንቀት በአንድ ጊዜ ወረሰኝ ።

የት ይሆን ያመጡኝ ? እጅ እግሬንስ ማሰር ለምን አስፈለገ ? ምን ጥፋት አግኝተውብኝ ይሆን ? እንደዚህ የሚታሰር ሰው መጨረሻው ምን ይሆን ? ጭንቅላቴ ጥያቄ በላይ በላዩ ያፈልቅ ጀመር። ለአንዱም ግን መልስ ማግኘት አቃተኝ።

ውልደቴ አዲስ አበባ ይሁን እንጂ እድገቴ ሙሉ ለሙሉ ደብረ ዘይት ነው። እዚያው አየር ሀይል ደጃፍ ላይ አየር ሀይሎችን እያየሁ አደግሁ ፤ ከዚያም እዚያው አየር ሀይል ተቀጠርኩ። አለቀ። ወደ ግራ ወደ ቀኝ የሞከርኩት ነገር የለም።

በ 1983 ዓ .ም . ለበረራ ሙያ ወደ ቀድሞዋ ሶቭየት ህብረት ለስልጠና ስላክ የነበረኝ ደስታ ወሰን አልነበረውም።ተስፋዬ ሁሉ እሩቅና ጥልቅ ነበር።ከአመታት በኋላም አንድ የስልጠናና አንድ የውግያ አውሮፕላን የበረራ ትምህርቴን አጠናቅቄ ወደ አገሬ ስመለስ ከአሁን በኋላ የአገር ሀብት ነኝ ብዬ ነበር።ብዙ ወጪ ወጥቶብኛላ ! ።

በተፈጥሮ ባህሪዬም ጠንቃቃ ሊያሰኝ የሚችል ቁጥብ ብሆንም ፤ ከጓደኞቼና በአጠቃላይ የስራ ባልደረቦቼ ጋር ስቆ ተጫውቶ ከመዋል በስተቀረ ወንጀለኛ ወንጀል ደፍሮ የሚሰራ ልብ የለኝም ። አደገኛ የሚባል ስብዕናም አልተላበስኩም።

ወያኔ አገሪቱን ተቆጣጥሮ የአየር ሀይልን በረራ ት /ቤት “ሀ” ብሎ ስራውን ሲጀምር በበረራ አስተማሪነት አገልግያለሁ ። እያደርም እስከ ሃላፊነት ። የምሰራው ለወያኔዎች ሳይሆን ፣

ለኢትዮጵያ ነው ብዬ አስብ ነበር ። እያደር ግን የአንድን ብሄር ብቻ መርጦ ወደ በረራ ስልጠና የማምጣቱ አካሄድ ባይዋጥልኝም፤ ሙያዬን ገና "ሀ" ብዬ መጀመሬ ነበርና እስኪ ትንሽ ልሥራ ፤ ነገሮችም ይቀየሩ ይሆናል በሚል ተስፋ ቀናቶች ተቆጠሩና አመታትን ወለዱ።ዛሬ ዛሬ ግን ከወያኔዎች ጋራ ውዬ ባደርኩባቸው ጊዚያቶች አገሬንና ህዝቤን ከድቼ የነበረ ዓይነት ስሜት ይሰማኛል።

እዚህ ጨለማ ቤት ውሥጥ ሆኜ በሰከንድ ውሥጥ ከውልደቴ እስከዚህች ደቂቃ ድረስ ያለችውን ጊዜ በአይነ ህሊናዬ ዳሰስኩት።ከፍርሃት በላይም ሃዘን አጥንቴን ዘልቆ ተሰማኝ።

እስርን በበረራ ተማሪነት ዘመኔ ከጓደኞቼ ጋር የዲሲፕሊን ጥፋት አጥፍተን ስንገኝ ከእነጓደኞቼ ለአንድ ቀን ወደ ከተማ እንዳንወጣ የመጠበቅ አይነት በአንድ ቦታ እንውላለን ፣ እናድራለን ። ያንን ታድያ እሥር እንለው ነበር ።

ዛሬ ግን ሰማይ የተደፋብኝ ያክል ተሰማኝ ። ከሰላማዊ ህይወቴ በአንድ ጊዜ ድቅድቅ ጨለማ ውሥጥ የፈጢኝ ታስሮ መገኘት ምን ይባላል ?

ለምን ያክል እዚህች ጨለማ ክፍል ውስጥ እንደቆየሁ መገመት ቢያቅተኝም ፤ እዚያው የቆምኩበት ሳሰላስል ሌሊቱ ተገባድዋል ። እርግጠኛ ነኝ ከምድር በታች የተሰራች ክፍል ውስጥ ነኝ ። ቀስ በቀስ ውርጭ መሰል ቅዝቃዜ ተሰማኝ ።

ጠዋት ከቤቴ ስወጣ የግንቦት ጀንበር ክርር ብላ ታቃጥል ነበርና ጃኬት እንኳ አልደረብኩም ። ከውስጥ ከአንዲት ስስ ካኒተራ በስተቀር ከላይ የበረራ ቱታ ነው የለበስኩት ። ቅዝቃዜው ጀርባዬን እየጨመደደኝ ቢመጣም ደንታ አልነበረኝም። እግሬን ድንዝዝ ብሎኝ ለረዥም ሰዓታት መቆሜን ይነግረኛል ። ከአንዲት ቦታ በፍፁም አልተንቀሳቀስኩም ። ጭንቅላቴ ሊፈነዳ ደርሷል ።

ጫማዬን፣ ቀበቶዬን አስወልቀውኛል ። በኪሴ ውስጥ የነበረች ብጣሽ ወረቀት እንኳ አልቀረችም ። ሰዓቱ ስንት እየሆነ እንዳለም መገመት በፍጹም አልቻልኩም ። ለነገሩ ግድም አይሰጠኝም ። የእኔ ጭንቀት ምን ያደርጉኝ ይሆን ነው ።

በደርግ ዘመን የወጣቶች የእስር ቤት ውስጥ ድብደባ በእራሴ ላይ ባይደርስም በቅርብ እያየሁትና እየሰማሁት ነው ያደግኩት ። የፈለጉትን ያድርጉኝ ፤ ብቻ እንዳይደበድቡኝ ነው ፀሎቴ ።

ሰው የት እንደገባሁ ያውቅ ይሆን ? ከሁሉም በላይ እናቴና ፍቅረኛዬ ታወሱኝ ። በይበልጥ እናቴ የልብ ህመምተኛ ናት ። መድሃኒት ለአንዲት ቀን አይደለም ሰዓቱን እንኳ ብታሳስት ህይወቷ አደጋ ላይ እንደሚሆን በሀኪሞች ተነግሯታል ። ትንሽ ነፍሷ እንዲቆይልኝ እማላደርገው ነገር የለም ። አሁን ታድያ ምን ይውጣት ይሆን ? የእኔን መሰወር ሰምታ የመድሃኒት መውሰጃ ሰዓቷን መከታተል ታቆም ይሆን ? ለህይወቷስ መጥፋት እኔ ሰበብ እሆን ይሆን ? .................. . በጭንቀት እራሴ ዞረ።

ይህንኑ በማሰላሰል ብቻ ከአንድ ቦታ በፍፁም ሳልንቀሳቅስ ለረዥም ሰዓታት ቆምኩ ።

በመጨረሻ ግን የሆነ መስኮት ነገር ተከፍቶ ወዲያው በፍጥነት የመዘጋት አይነት ድምፅ ተሰማኝ ። ወደ ውስጥ የገባ ነገር እንደሌለ በማዳመጥ አረጋገጥሁ ። አልፎ አልፎ የኮቴና የመንጓጓት ድምፅ ይሰማኛል። ወዲያው ግን እረጭ አለ ። እግሬን በማንቀሳቀስ ትንሽ ወዲህና ወዲያ እንዳልል እንኳ ምን ታይቶኝ ? ድንግዝግዝ ያለ ጨለማ ወርሶኛል ። ከአሁኑ ሞቴን መረጥኩ ። ሊመጣ የሚችለው መንገላታት ከአሁኑ አሳሰበኝ ።

በእርግጥ ምግብ ከቀመስኩ 24ሰዓት ሳይሆነኝ አይቀርም ። እያቅለሸለሸኝና እያጥወለወለኝ ነው ። አሁን አሁን ያለሁበት ክፍልም ሽታ እንዳለው እየታወቀኝ ነው ። ቀስ እያልኩም ከምናምን ጋራ እንዳልጋጭ እጄን ወደፊት ዘርግቼ ለመራመድ ሞከርኩ ። እግሮቼ በአንድነት ተያይዘው በሰንሰለት ታስረዋልና በእግሬ ጣቶች መሬቱን እየቆነጠጥኩ ለመንሸራተት መሞከር እንጂ መራመድ የማይታሰብ ሆነ ። እንደምንም እየተንፏቀኩ ግድግዳ ጋ ደረስኩ ። ወደ ግድግዳው በተጠጋሁ ቁጥር ግን ሽታውና ክርፋቱ ባሰብኝ ። ይሁን እንጂ በታሰሩት ሁለት እጆቼ ግድግዳውን እየዳሰስኩ ዙርያውን ለመቃኘት ሞከርኩ ። ከባድ ነው ። መነቃነቅ አቃተኝ ። በመቆም ብዛት በደነዘዘው እግሬ የትም መድረስ አልቻልኩም ። ተሥፋ መቁረጥ ግን አልፈለኩም ። መዳሰሴን ቀጠልኩ ። ያለሁባት ክፍል እጅግ ጠባብ ናት ። ግድግዳው ብሎኬት ዓይነት ይሰማኛል ። የተፈረካከሰ ግድግዳ ነው ። መዳሰሴን ቀጠልኩ ። ድንገት ጄሪካን ነገር እግሬ ነክቶ ተደፋ ። ፈሳሽ ነገር ነው ። እጅግ መጥፎ ሽታ አለው ። ሽንት መሆን አለበት ። የተደፋውን ጄሪካን ለማንሳት አልቻልኩም ። በአንድ በኩል ግማቱ ፣ በሌላው ደግሞ እግሬ መታሰሩ ለማጎንበስ ሚዛኔን መጠበቅ አቃተኝ ። ምንም ማድረግ አልችልም ። የፈሰሰው ግማት ላይ በእግሬ መንሸራተቴን ቀጥያለሁ ። የብረት መዝጊያ ነገር ነካሁ ። በሩ መሃል ላይ ደግሞ ትንሽ መስኮት ነገር ያለው ይመስለኛል ።

እቃ ማስቀመጫ ትንሽ መደርደሪያ ነገር አለው ። ኩባያ ነገር ከተቀመጠበት በእጄ ነክቼው ተደፋና መሬት ሲሚንቶው ላይ ሲወድቅ አገሩን በጩሀት በጠበጠው ። ክው ብዬ ደነገጥኩ ። ያልጠበቅኩት ድምፅ ነበርና እኔኑ መልሶ አስደነገጠኝ ። ሁኔታውንም እስከማገናዝብ የልቤ ምት ጨመረ ።

እንዲሁ እያልኩ ያለሁባትን ክፍል በዳበሳ ጨረስኳት ። እጅግ ጠባብ ነች ።

ወለሉ ላይ የፈሰሰው ሽንት መሰል ነገር ግማታም ፈሳሽ ምን አልባትም እዚህች ጠባብ ክፍል ውሥጥ ሌላ የእኔ ቢጤ ይኖር ይሆን የሚለውን ጥያቄ በአእምሮዬ ውሥጥ አጫረው ። በአይኔ ማየት ባልችል ፣ አንዳች ኮሽታ ድምፅ በማጣቴ ብቻዬን መሆኔን አረጋገጥኩኝ ። ይሁን እንጂ እስከ ቅርብ ሰዓት ድረስ ሌላ ሰው ነበረበት ማለት ነው ።

ጭንቀቱና ጥርጣሬው እየባሰብኝ መጣ ። ከሁሉም በላይ በደርግ ጊዜ የነበረው የወጣቶች የጅምላ ግርፊያና ግድያ ታወሰኝ ።

እጅግ አሰቃቂ ዘመን ነበር ። ዛሬ ደግሞ እኔም በተራዬ እዚህ አደገኛ ክስተት ደጃፍ ላይ ሳላስበው ድንገት መገኘቴ መፈጠሬን አስጠላኝ ።

እስከ አሁን ማንም ወደ እኔ የመጣ የለም ። ከክፍሌ ውጪ ግን አልፎ አልፎ የመንጓጓት ድምፅ ይሰማኛል ። በሃሳብ ደንዝዤ ከአንድ ቦታ ሳልነቃነቅ ተገትሬ ባለሁበት ሰዓት ፤ የአለሁባት

ክፍል በር ተከፈተና ባትሪ የያዙ ሁለት ሰዎች ወደ ውስጥ በመግባት ግራና ቀኝ ደግፈውኝ ወደ ውጭ እንድራመድ ትእዛዝ ሰጡኝ ።

መንፈሴ መሰበር ጀምሯል ። የመብላት ፍላጎት አይኑረኝ እንጂ ምግብ አለማግኘቴም አድክሞኛል ። ሃሳቡ ፣ ጭንቀትና ፍርሃቱ በአንድነት ተባብረው መንፈሴንም አካሌንም ስብርብር አድርገውታል ። በተስፋ መቁረጥ ዝም ከማለትና የሚሉኝን ከማድረግ በስተቀር ቃል አልተነፈስኩም ።

በሁለት ሰዎች እንደተደገፍኩ ከአለሁባት ክፍል ቀጥላ ወደ አለች ሌላ ክፍል ውስጥ አስገቡኝ። ክፍሏ ጠበብ ያለች ነች ።ደብዘዝ ያለ መብራት በርቶባታል ። ውስጧ ንፅህናዋ የተጠበቀ አይደለም ። ቆሸሽ ካለ ጠረጴዛ ጅርባ አንድ ሰው ተቀምጧል ። ጥቁር ነው ። ከርዳዳ ፀጉሩ የተበጠረ አይመስልም ። ግዙፍ ሰውነቱና የደፈረሰው አይኑ ሰላም አይሰጡም ። ምንም ሳይተነፍስ ዝም ብሎ አተኩሮ ያየኛል ። ከጎኑ የቆመ ቀላ ያለ ቀጭን አጭር ሰው አለ ። ሁለቱም አተኩረው ያዩኛል ።

ግራና ቀኝ ደግፈው ያመጡኝ ስዎች ውስጥ ካሉት ጋራ በትግርኛ ቋንቋ ከተነጋገሩ በኋላ ክፍሏን ለቀው ወጡ ። ከበሩ አጠገብ ካለች ቆሻሻ ወንበር ላይ እንድቀመጥ ቀዩ አጭሩ ሰውዬ ምልክት ሰጠኝ ። ቀጥሎም ማን እንደሆንኩ የህይወት ታሪኬን እንድነግረው ጠየቀኝ ። አጠር አጠር አድርጌ ደብረ ዘይት ከተማ ማደጌን፤አየር ሀይል መቀጠሬን ፣ ለበረራ ሙያ የቀድሞዋ ሶቭየት ህብረት መላኬንና ከደርግ መሸነፍ በኋላም በበረራ አስተማሪነት እያገለገልኩና የጀት በረራ ስልጠና ስኳድሮን አዛዥ መሆኔን ሁለት ደቂቃ ባልበለጠ ጊዜ ጠቅለል አድርጌ ነገርኩት። ለተወሰነች ደቂቃ ትኩር ብለው ስያዩኝ እኔም ምን ሊከተል እንደሚችል በመጓጓት መልሼ አይን አይናቸውን እያየሁ ሳለ አሁንም ቀድሞ ጥያቄ ያቀረበልኝ ቀዩ አጭሩ ሰውዬ እዚህ እንድመጣ ያደረገኝን ጥፋት እንድናዘዝ ይጠይቀኛል። እኔም በመመለስ እስከ አሁን ጥፋቴ ግልፅ እንዳልሆነልኝና አጥፍተሃል የምባለው ነገር ካለ ግን ቢነገረኝ ለመናዘዝ ዝግጁ መሆኔን አሳውቅሁ ። ሁለቱም እርስ በእርሳቸው እየተያዩ የለበጣ ፈገግታ ተሰጣጡ። የተናገርኩትን ያለማመን ሁኔታ መግለጫ ሆኖ ተሰማኝ ። አንድ ሁለት ቃላት በትግሪኛ ተነጋገሩና ያው የሚያናግረኝ የነበረው ሰውዬ “ እኛ የምንነግርህ ምንም ነገር የለም እራስህ በፈቃደኝነት ብትናዘዝ የሚሻልህ ይመስለኛል፤እምቢ ካልክ ግን ምርጫው ያንተ ነው “ የሚል የማስፈራራት ቃና ባለው አይነት ተናገረኝ ። ቶሎ ብዬ እራሴን ፈተሽኩ ። ምን አድርጌ እንደሆነ አወጣሁ አውረድኩ ግን ጥፋት ነው የምለው ምንም ነገር አንዳልፈፀምኩ እርግጠኛ ሆንኩ። በመሆኑም እኔ ከሰላማዊ የዕለት ተዕለት ተግባሬ ላይ በማላውቃቸው ሰዎች ታፍኜ እንደመጣሁና አጥፍቻለሁ የምለው ምንም ነገር ትዝ እንደማይለኝ በእርግጠኛነት ተናገርኩ ። አሁንም ሁለቱ በትግሪኛ ተነጋገሩና ከዚያም ወደ እኔ በመዞር በሰላም ሁሉንም እንድትነግረን እድል ተሰጥቶህ ልትጠቀምበት ፈቃደኛ አልሆንክም ስለዚህ የ 24 ሰዓት ጊዜ እንሰጥሃለንና ተጠቀምበት ብለው ደግፈው ያመጡኝን ሰዎች ጠርተው በተለመደው የትግሪኛ ቋንቋ የሆነ ነገር ብለዋቸው በመጣሁበት ዓይነት እግሬን የታሰርኩበት ሰንሰለት እንደልብ ስለማያራምደኝ ግራና ቀኝ ደግፈው ቀስ እያልኩ እየተራመድኩ ወደዚያች መልኳን እንኳ በእርግጥ ወደ ማላውቃት ጨለማ ክፍሌ መልሰውኝ በሩን በጀርባዬ ቆለፏት።

በእርግጥ ነገሩ ጠጠር ብሏል ማለት ነው ።አንድ ነገር ግን መላልሶ ቅር ያሰኘኝ ጀመር ። አገሪቷን እንደፈለጉ እያደረጉ ያሉት ትግሪኛ ተናጋሪዎች መሆናቸውን ከተረዳሁ አመታት ያለፉኝ ቢሆንም እንደዚህ ግን ሁሉንም ጉዳይ ፈላጭ ቆራጭ መሆናቸው በእጅጉ አሳዘነኝ ።

ኢትዮጵያ የማን ናት ? እኔስ የማን እሆን ይሆን ? መልስ ላገኝለት አልቻልኩም።

ድሮ ድሮ ልጅ ሆኜ ደብረ ዘይት ከተማ ከትግራይ ቤተሰብ የተወለደ የቅርብ ጓደኛ ነበረኝ። አብረን ውለን እናድራለን።አብረን አንድ ክፍል ውስጥ ቁጭ ብለን ተምረናል።እነሱ ቤት ሄጄ እበላለሁ እጠጣለሁ፤ እሱም በተራው እኛ እቤት እየመጣ ይበላል ይጠጣል።አንድም ቀን ትግሬ መሆኑ ትዝ ሳይለኝ አንድ ላይ ስራ ገብተናል።

በአየር ሀይል ቆይታዬም ውስጥ እጅግ ቅርበት ያለን፣ ለአንድ ድቂቃ እንኳ መለያየት የሚያቅተን ቤተሰቦቻቸው ትግሬዎች የሆኑ ጓደኞች አሉኝ ። በሰላም እንኖራለን ።

አሁን እየደረሰብኝ ባልው ሁኔታ ግን ስሜቴ ደፈረሰብኝ ። ከስራ ቦታዬ እያታለሉ አቆይተው ያሳፈሩኝ ትግሬዎች ነበሩ ። በመኪና አፍነው ወደዚች ጨለማ ክፍል ያመጡኝም ትግሬዎች ናቸው ። ከአለሁባት ጨለማ ክፍልም እየገፉ ቢሮ መሰል ነገር ውስጥ ያስገቡኝም ትግሬዎች ናቸው ። ጥፋቴን ተናዘዝ እያሉ የሚያስለፈልፉኝም ትግሬዎች።እንዴት ነው ይህች አገር ያለ ትግሬ ውላ ማደር አቃታት ማለት ነው ? ይህች አገር የትግሬዎች ከሆነችስ ታድያ የእኔ አገር የት ነው ?

ለምን ያክል ሰዓት አንድ ቦታ ቆሜ በሃሳብ እንደምብሰለሰል መገመት አልቻልኩም እንጂ መቀመጥ ከነመኖሩም ረስቼዋለሁ ።ጋደም እንኳ ለማለት የክፍሏን ዙርያ በዳበሳ ባስስ ምናምኒት ጨርቅ እንኳ ማግኘት አልቻልኩም።

አሁን አሁንስ ረሃቡም በቅጡ እንዳላስብ እያደረገኝ ነው። ድክምክም ብያለሁ ። በዳበሳ በሩ ላይ ካለው መደርደሪያ ነገር ላይ ቁራሽ ዳቦ ነገር አገኝሁ ። ለካስ በበሩ መሃል ባለችው ማሸንቆሪያ ነገር ደረቅ ዳቦ ይጥሉልኛል ።ይሁን እንጂ የቤቱ ግማት እህል ለመብላት አይደለም ለመተንፈሱም ይግድ በመሆኑ እንጂ አይቻልም። አሁን ግን አማራጭ የለም ። እጄ ሁሉ ቆሽሿል ። በሽንቱም በዳበሳውም እንዳልነበረ ሆኗል።ግን ዳቦዋን በታሰሩት ሁለት እጆቼ መሃል ይገቼ አንድ ሁለቴ በጥርሴ እየገመጥኩኝ አኝኬ ለመዋጥ ሞከርኩ ። ከዚያ በላይ ግን መውሰድ አልቻልኩም ። ለካስ ውሀም ያስፈልገኛል ፤ ማግኘት ግን አልቻልኩም ። በጥም ተቃጠልኩ ።

አካሌ በመዛሉ ግድግዳ ተደግፌ ቁጢጥ አልኩኝ ። ቅዝቃዜውም እየበረታብኝ መጣ ። በዚህ ዓይነት እየተሰቃየሁ እያለሁ ያለሁበት ክፍል በር ተከፈተ ። ወደ ውስጥ ገበተው ይዘውኝ ወጡ ፤ ሽንት መሽናት እንደምፈልግ ነገርኳቸው ። ነገር ግን ውስጥ ጄሪካን እንደነበረልኝ ከመጠቆም በስተቀር ያደረጉልኝ አልነበረም ። በቀጥታ ከጐኔ ወደ አለች ክፍል ሊያስገቡኝ የበሩን ደፍ እንዳለፍኩኝ ሃይለኛ ቡጢ ሰውነቴ ላይ አረፈ ።

ተሽከርክሬ ወደቅሁ ።በኤሌክትሪክ ገመድ ዓይነት ክፉኛ ገረፉኝ ፤ የጠየቁኝ ነገር የለም ። እንድናገርም ምንም ጊዜ አልሰጡኝም ። ውስጥ እግሬን፣ ውስጥ እጄን፣ ጀርባዬን ይገርፉኛል። ተቃጠልኩ ። በመጨረሻ ግን እራሴን ሳትኩ ።ስነቃ እንደዝያው እጅ እግሬ በታሰረበት አኳኋን ወለል ላይ ተዘርሪያለሁ ። እሬሳዬ እንጂ በህይወት ከዚህች ክፍል እንደማልወጣ እርግጠኛ ሆንኩ ። ለሁለተኛና ለሶስተኛ ጊዜም እንዲሁ እየተሸከሙ ወስደው መፈጠሬን እስክጠላ ገርፈውና ቀጥቅጠው ይመልሱኛል ።የለበስኳትን የበረራ ቱታ በላዬ ላይ ቦጫጨቂዋት ። እግሬና ጀርባዬ ክፉኛ ቆሰለ ።በጣም አዘንኩ ፤ በጣም አለቀስኩ ። ጥፋቴን እንኳ አውቄ በሆነ

EthioLion.Com

ኖሮ ደስ ባለኝ። ግን ምን ተገኝቶብኝ ይሆን ?

የፈለገውን ጥፋት አጥፍተሃል ቢሉኝ እንኳ፣ ለዚህ ቅጣት የሚያደርስ ወንጀል የሚሰራ ልብም ስብዕናም እንደሌለኝ ለራሴ እርግጥኛ ሆንኩ ። ትግሬ ይሁን ወያኔ ጠላቴ የትኛው እንደሆነ ለመለየት ተሳነኝ ። ሁለቱንም ግን በጅምላ እንድጠላ ውስጤ ጥንስስ ተጠነሰሰ። ስንቱ ኢትዮጵያዊ በወያኔና በትግሬ መከላከል ያለውን ልዩነት እንዳያይ አድርገውት ይሆን ? ቤት ይቁጠረው ......... . ።

ከአሁን በኋላ ለእራሴ እራሴው ካልሆኩኝ በስተቀር ማንም ሊያስታምመኝም ሊያድነኝም እንደማይመጣ አረጋግጫለሁ ። ስለዚህ በረሃብ ብዛት ሰውነቴ ላይ ያሉ ደምስሮች ሁሉ መንዘር ጀምረው ከፍተኛ ህመም ፈጠሩብኝ ። ሆዴን ሳይሆን ንዝረቱን ማቆምና ማስታገስ ነበረብኝ ። በሆዴ እየተሳብኩ በዳበሳ የማገኛትን ደረቅ ዳቦ በምራቄ እያራስኩ መቀማመስ ጀመርኩኝ ።

አሁን አሁን በቀን አንዴ ዳቦና ኩባያ ውሃ በበሩ አሸንቁረው ያስቀምጡልኝ ጀመር። ማንንም አላይም፤ እነሱም ወደውስጥ መግባት አይፈልጉም ። በቀን አንድ ጊዜም እዚያው ኰሪደር መሰል መተላለፊያ ውስጥ ባልች ሽንት ቤት ውስጥ መፀዳዳት ጀመርኩ ። የሚገርመው ግን የእጄንም ሆነ የእግሬን ሰንሰለት ያለመፍታታቸው ነው ። በምፀዳዳበት ጊዜ እግሬ በመታሰሩ ምክንያት ሚዛኔን ጠብቄ መቀመጥ አልቻልኩም ። እጄ በመታሰሩ ደግሞ ሱሪዬን መፍታት እንኳ ብችልም መልሶ ለመታጠቅ ግን ፈፅሞ የማይታሰብ ነው ። ይሄ ደግሞ እጅግ ቅስም ይሰራል ::

በዚህ ዓይነት አሰቃቂ አኳኋን በግምት ለአንድ 20 ቀናት እንደቆየሁ አንድ ቀን ከለመድኩት ሰዓት ውጪ የክፍሌ በር ተከፍቶ ሁለት ሰዎች እየተጣደፉ በመግባት ግራና ቀኝ ደግፈው አይኔን በመሸፈን ይዘውኝ በመውጣት መኪና ላይ ጭነውኝ መንገድ ቀጠልን ።

ይዘውኝ የሚሄዱትን ሰዎች ቁጥራቸውን በውል ባላውቀውም ከሁለት በላይ ናቸው። ዘና ያለ ወሬ የያዙ ይመስላሉ ። የሚጠቀሙት ያው የተለመደውን ትግሪኛ ነው ። ልቤ እጅግ ቢፈራም የማመጣው ነገር ማለመኖሩ ተሰፋ ቆርጫለሁ ። አሁን እኔነቴ ብዙውን በድን ሆኗል ። በልቤ እፀልያለሁ ።

ከውጪ የሚገባው አየር ቀዝቃዛ ነው ። ያፈኑኝ ዕለት ግንቦት መጨረሻ ደረቅና ሞቃታማ እንደነበር አስታውሳለሁ ።አሁን ክረምቱ እየገባ መሰለኝ ። እንደ ግምቴ ከሆነ አሁን ሰኔ ሳይጋመስ አይቀርም።
እርግጠኛ ነኝ ከ 30-40 ደቂቃ በላይ ተጉዘናል ... .. መጨረሻ ግን መኪናዋ ሙሉ ለሙሉ ቆመችና ግራና ቀኝ ደግፈውኝ ወረድኩ ። ከሆነ ሰው ጋርም በትግሪኛ ተነጋግረው ወደ ሆነች ክፍል ገፍተው ካስገቡኝ በኋላ አይኔ የተሸፈነበትን ጨርቅ ገልጠውልኝ በሩን ከጀርባዬ ቆልፈው ድምፃቸው እየራቀኝ በመምጣቱ መሄዳቸውን ገመትኩኝ ።

የአሁኗም ክፍሌ ጠባብ ናት ...... እንዲያውም ከበፊቱ በጣም የምትጠብ ይመስለኛል። ምክንያቱም በዳበሳ ስቃኛት ጊዜ አልፈጀችብኝም ። ቅዝቃዜዋ ግን አይጣል ነው ። ከበሩ በላይ ባለች የአየር ማስገቢያ ቀዳዳ በኩል ቀዝቃዛ ንፋስ ወደ ውስጥ ይነፍሳል ... . ወለሉን ስዳብስ ፎጣ መሳይ ጨርቅ ነገር ከአንደኛው ማዕዘን ላይ ተዘርግቷል። አሁን አሁን

EthioLion.com

እስካልደበደቡኝ ድረስ ተመስገን ማለት ጀምሪያለሁ ።ለረዥም ሰዓታት አንድ ቦታ ቆምኩኝ …… ይሁን እንጂ ቅዝቃዜውን መቋቋም አቃተኝ … .. አጥንትን የሚሰብር ብርድ ተሰማኝ ። ስለዚህም እዚያች ፎጣ መሳይ ብጣሽ ጨርቅ ነገር ላይ ኩርምት ብዬ ቁጭ አልኩኝ።

የተለመደው የዝምታ ኑሮ በአዲሷ ጠባብ ጨለማ ክፍሌ ውስጥም ቀጠለ … . የሚያናግረኝ የለም … . እንዲህ አጥፍተሃልም የለም … እንዲሁ ዝም ዝም ብቻ ።ክፍሏ ውስጥ በእግሬ በመራመድ እንኳ እንቅስቃሴ እንዳላደርግ አንደኛ ክፍሏ ጨለማ የወረሳት ናት ፤ ሁለተኛ ጥበቷ ብዙም ሊያንቀሳቅስኝ አይችልም… . ከሁሉም በላይ ግን የእግሬ በሰንሰለት መታሰር ሁሉንም እርግፍ አድርጎ ከመተው በስተቀር አማራጭ እንደማይኖር ይነግረኛል ።

አሁን አሁን በቀን አንድ ዳቦ ሊጥሉልኝ ከበሩ በታች በተሰራች ጠባብ መስኮት ነገር ከፊት አድርገው በፍጥነት ሲዘጓት ይሰማኛል ።አካባቢዬ ሁሉ እረጭ ያለ ፀጥታ የወረሰው በመሆኑና ቅዝቃዜውም እየከበደኝ በመሆኑ ከእነ ህይወቴ የተቀበርኩ እየመሰለኝ መጣ ። ይህንን ቅዝቃዜና ዝምታ መቋቋም እንደማልችል ከውዲሁ ለእራሴ ነገርኩት …… አሁንም እንደበፊቱ እኩለ ሌሊት ግድም ይመስለኛል ( ሰዓት መለየት በእጅጉ ጠፍቶብኛል )… . እዚያችው ከጠባቡዋ ክፍሌ ጉን በተሰራች ሽንት ቤት እንድጠቀም ያደርጉኛል ………… ..ባትሪ የያዙ ሰዎች ከመሆናቸው በስተቀር አንድም ጊዜ ፊታቸውን ለማየት አልታደልኩም ። እርስ በእርሳቸው ሲነጋገሩ ግን የትግሪኛ ቋንቋ መሆኑን አረጋግጫለሁ ።

ከዚህ አሰቃቂ መከራ ልገላገል የምችለው ግን በአንድ መንገድ ብቻ መሆኑን አምኛለሁ …… .. ያም እራሴን ማጥፋት ብቻ …… .

በምን እራሴን ላጠፋ እንደምችል ግን ማግኘት አቃተኝ ። ብዙ ሰዎች በቅርብ ከማውቃቸው ጭምር ጥሩ ህይወት እየነበራቸው በወጣትነት ዘመናቸው እራሳቸውን አጥፍተዋል ። ታድያ ለእኔ እዚህ ጉድጓድ ውስጥ በህይወት ተቀብሮ ነፍሴ እስከምትወጣ ከመጠበቅ በስተቀር ቆይቶ ለማይቀርልኝ ሞት ከውዲሁ ስቃዬን ለማሳጠር ወሰንኩ።

እጄም እግሬም በሰንሰለት የታሰረ ከመሆኑም በላይ ይሄነው ይምለው እራሴን በቶሎ ለማጥፋት ልጠቀም የምችልበት ነገር አጣሁ…… .. አንድ አማራጭ ግን አለ ፤ ይኸውም ምግብ ማቆም ብቻ ነበር ።

አንድ ቀን በጣም ሆድ ብሶኝ እያለቀስኩ ፀለይኩ ……… በህይወት ዘመኔ እግዚአብሄርን አስቀይሜውለሁ ብዬ የማስባቸውን ጥቃቅን ነገሮች ሳይቀሩ በማስታውስ አምላኬን ይቅርታ ጠየቅሁ ። ከዚያች ቀን ጀምሮም አንዳችም ከሚሰጡኝ ዳቦ ላለመቅመስ ወሰንኩ ።

እርግጠኛ ነኝ ሶስት ቀን ያለምግብ ያሳለፍኩ ይመስለኛል ። ምግብ ስለማልውስድ ነው መሰለኝ ውሃ በፍፁም ትዝ ብሎኝ አያውቅም …… . ርቦኝ ርቦኝ… .. ሆዴም ጮሆ ጮሆ መጨረሻ ላይ ትቶኛል ። ሙሉ ለሙሉ የመብላት ፍላጎቴ ጠፍቷል…… .እየደከምኩና እንቅልፍ እንቅልፍ እያለኝ መጣ ።ምን አልባት አራተኛው ቀን ይመስለኛል ሰውነቴን ሁሉ ይነዝረኝ ገባ ። ቊንቅላቴን ፣ እጆቼን ፣ አንገቴ አካባቢና አይኔ አካባቢ ያለውን ሁሉ ንዝረት መቋቋም አቃተኝ ። የህመም ስቃዬን ማስታገስ ነበረኝ ፤ በሩ ስር ሁልጊዜ በዳበሳ ከማገኛት ኩባያ ውስጥ ያገኘሁትን ውሃ በአንድ ትንፋሽ አንስቼ ጨለጥቁት ። ላብ ነገር እንዳጠመቀኝ

ትዝ ይለኛል ። በተረፈ ለረዥም ጊዜ እዚያች ቀዝቃዛ ሲሚንቶ ላይ በተዘረጋች ብጣሽ ፎጣ መሳይ ጨርቅ ላይ ኩርምት ብዬ ተኛሁ ።

ስነቃ እጅግ እርቦኛል ...... . ምንም ማድረግ አልቻልኩም ፤ በዳበሳ መሬት ላይ ያገኘሁትን ዳቦ አንስቼ መብላት ጀመርኩ ። ከመጀመሪያው ቀን የበለጠ ድምፅ አውጥቼ ስቅስቅ ብዬ አልቅስኩ ። መብላቴን ፣ መሸነፌን አልወደድኩትም ...... ምክንያቱም የጊዜ ጉዳይ እንጂ ከዚህች ክፍል እሬሳዬ እንደሚወጣ እርግጠኛ ሆኛለሁ ። እስከዚያች እለት ያለውን ስቃይና መከራ ማንም ሰብዓዊ ፍጡር አይችለውም ።

በሌላ ጊዜም ሁለት ሶስቴ ምግብ ለማቆም ሞከርኩ ......ግን ያው ነው ... ያንን ንዝረትና ህመም ተቋቁሜ ማለፍ ተሳነኝ ።

ዛሬ ዛሬ እነዚህ ጅቦች እጅ ከገባሁ 4-5 ወራት እየሆነኝ ይመስለኛል ... .. ከወደ መሃል አናቴ ጀምሮ ወደ ግምባሬ እየሳሳ የመጣው ፀጉሬ እንኳ ጉፍሯል ። በአየር ሀይል የረዥም ጊዜ ቆይታዬ ምክንያት ፀጉሬ ከአንድ ሳንቲም በላይ አሳድጌ አላውቅም ...... .. የአሁኑ ግን ጉድ መስሎ ተሰማኝ ፤ የፊቴ ላይ ፀጉርም እንደነገሩ አድጓል ። በይበልጥ የአገጭ ፂሜ መተከዣ ከሆነኝ ሰንባብቷል ።በሰንሰለት የታሰሩ ሁለት እጆቼን ደረቴ ላይ በማሳረፍ በቀኝ እጄ ጣቶች የአገጩን ፂም ሳብ ሳብ እያደረግሁ በሃሳብ እርቄ እሄዳለሁ ።

በየሰከንዱ ግን እናቴ ፊቴ ላይ ድቅን ትላለች ... .. እየተቀጣሁ ያለሁት እኔ ብቻ እንዳልሆንኩ ይሰማኛል ...... ምንም ወንጀል የሌለባት አዛውንቷ እናቴም በሰቀቀንና ስጋት እየተቀጣች መሆኑ ይሰማኛል...... በእኔ ምክንያት ህይወቷ ያልፍ ይሆን ? ወይኔ ጉዴ ! ... .. ወንጀለኛነት ይሰማኝ ጀመር ፤ አልፎ አልፎም እጅግ የምወዳትን ፍቅረኛዬን አስባለሁ ...... . ድንገት ነው እንደወጣሁ የቀረሁት ፤ ሊያሶሩብኝ የሚችሉትን የወንጀል መዓት ብትሰማ ታምናቸው ይሆን ? እላለሁ ።ላታምን የማትችልበት ምክንያት አይኖርም ... ፍቅረኛዬ እንጂ እናቴ አይደለች ፤ ... . ?

በእልህ ጥርሴን እነክሳለሁ ... ..እየሞተ ባለው አካሌና መንፈሴ ቂም እቋጥራለሁ ። እዚያችው ጉድጓድ ውስጥ እንደምሞት እርግጠኛ እየሆንኩ እንኩዋ እናቴን ያለውንጀሏ እየቀጣብኝ ያለውንና ፣ የወደፊት ሚስቴን እየቀማኝ ኑሮዬን እያፈረሰ ያለውን ወያኔ ቂም እንደቋጠርኩበት ነው ።

ውሃ ለሰውነት መታጠቢያም እንደሚያገለግል አሳሪዎቼ ጋ የሚታወቅ አይመስለኝም ... .. ግና ለሚሞት ሰው መታጠብ ምን ሊያደርግለት?

እውነቴን ነው የምላችሁ ሰውነቴን አይደለም ፊቴን ታጥቤ አላውቅም ... . ጥርስ መቦረሽ ምናምን የሚባሉት እዚህ ያለሁበት ስፍራ በፍፁም አይታወቁም ።

የለበስኳቸው የውስጥ ካናቴራና ፓንቴ እላዬ ላይ በመበታተናቸው ቀድጄ ካላዬ ላይ አውልቄ ከጣልኩ ሰንብቻለሁ ... .. የበረራ ቱታዬ የቀንም የሌሊትም ልብሴ በመሆኑ ጉልበቴ ላይ ፣ ከኋላዬ ፣ ትከሻዬ ላይ ፣ በተጨማሪም እግሬና እጅጌዬ ጫፍ ጫፍ ላይ ተቀዳዷል ። እራሴን ማየት ባለመቻሌ እንጂ ጥሩ እብድ መምሰሌን እርገጠኛ ነኝ ።

ቀስ በቀስ ግን አቅሜ በእጅጉ እየደከመ እየደከመ ህመም ይሰማኝ ጀመር ...... . እንቅልፍ የሚባል ተኝቼም ስለማላውቅ ጭንቅላቴ ደንዝዞ ሰውነቴ ቅልል እያለኝ መጥቷል ፤ እንደቀድሞው ቆሞ ማደርና መዋል አቃተኝ ... ሚዛኔን በፍፁም መጠበቅ የማይታሰብ ሆነ ። ከሁሉም በላይ ግን አንዳችም ድምፅ ስለማይሰማኝ .. የረዥም ጊዜው ዝምታ ጆሮዬ ላይ ኡኡኡኡ...... .የሚል ድምፅ ፈጠረብኝ ። ይህንን ድምፅ ከጆሮዬ ማስወገድ አቃተኝ ... ቀጥሎም የልቤ ምት ቀየረ ... . ይደክመኛል ። ብዙውን ጊዜም ትንፋሼ እየተቆራረጠ አስቸገረኝ ። መንገዴን እንደጀመርኩ እርገጠኛ ሆንኩ ።

ሞትን ብመኘውና ብፈልገውም እንደዚህ ዓይኑን አፍጥጦ ልወስድህ ነው እያለኝ ሲመጣ ግን ጉልበት ከዳኝ ... . እጅግም ፈራሁ ... . አዘንኩም ... .. ተስፋዬም ሙጥጥ ብሎ አለቀ ።

በዳበሳ ያገኘሁትንም በር መደብደብ ጀመርኩ ... ..ድምፄን ከፍ አድርጌም መጮህ ጀመርኩ ። የመጀመርያ ሁለትና ሶስት ቀን ምን እንደምፈልግ ጠየቁኝ ... . ወደ ሰው እንዲቀላቅሉኝም ተማፀንኳቸው ። ከውጪ ሳቅ ተሰማኝ ... . እየታዘቡኝ መሆኑ ነው ።

በሩን ድብደባዬን በታሰርኩበት ሰንሰለት ማደረግ ጀመርኩ ... . ብረቱ በር ከፍተኛ ድምፅ ያሰማል ... . እኔም በምችለው መጠን ኡ ..ኡ... ብዬ እጮሃለሁ ። አንዳችም ለውጥ አጣሁ ። እንዲሁ ስጮህ ማደርና መዋልን ስራዬ አደረግሁት ... እውነት ለመናገር ብዙሃኑን ምን እንደምል አሁን አላስታውሰውም ።

እዚች ቀዝቃዛ ክፍል ውስጥ ከ 6 ወራት ያላነሰ ያሳለፍኩ ይመስለኛል ። አንድ ቀን ያለወትሮው በሬ ተከፈተ ... . ቀዝቃዛ ላብ በጀርባዬ ሲወርድ ተሰማኝ ። ቁጥራቸውን ባላውቅም የእጅ ባትሪ የያዙ ሰዎች ወደ ውስጥ አበሩብኝ ... .. ኩርምት በዬ ቁጭ እንዳልኩኝ ነው ... .

ቆጣ ባለ ድምፅ ና ! ውጣ የሚል ድምፅ ተሰማኝ ... . ዛሬ የመጨረሻዬ መሆኑ ነው ። የተናገሩኝን ብሰማም ተግባራዊ ማድረግ እንዳለብኝ ግን አልመጣልኝም ... . ድንጋጤውም ከመጠን በላይ ሆኖብኝ ሊሆን ይችላል ። ኩርምት በዬ ቁጭ ባልኩበት ሁኔታ ጭንቅላቴን ወደ እግሬ ውስጥ መልሼ ደፋሁ ... . ከያዙት የእጅ ባትሪ የሚወጣውን ብርሃን አይኔ መቋቋም አልቻለም ።

ደጋግመው ና ! ውጣ... ተነስ ይሉኛል ... እኔ ግን ተነስቶ ለመቆም የሚችል ጉልበት አልነበረኝም... በኋላ ግን አንዱ መጥቶ እያመናጨቀ እጄን ከፍ አድርጎ ብብቴ ስር በመያዝ ሊያስነሳኝ ሲሞክር .. የግራ እጄን የቱታ እጅጌ ከትከሻዬ ጀምሮ ቀደደው ።

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ... .. ከዚችው እርቃኔን መሸፈን እያቃታት ካለች ጨርቅ ላይ ተጨማሪ እጅጌውን መንቀል ...... .. አሳዘነኝ ።

ደጋግፈው አወጡኝ ፤ እንደተለመደው አይኔን ሸፈኑትና እየተራመድኩ ስወጣ ግን ሰውነቴን ሰንጥቆ የሚገባ ቅዝቃዜ ተሰማኝ ። አጣድፈውም ቁመቱ ረዘም ያለ መኪና ላይ ጫኑኝ ። አንድ ሁለት መወጣጫ ረግጬ ነው በዳበሳ የመኪናውን በር እያስያዙኝ ወደ ውስጥ ገብቼ የተቀመጥኩት ።
ይመስለኛ ሁለት ሰዎች መሃል ነው የተቀመጥኩት ... .. አልፎ አልፎ በትግሪኛ ይነጋገራሉ ...



EthioLion.com

. ረዥም ጉዞ ተጉዘናል ፣ በየመሃሉም መኪናው ለአጭር ጊዜ ይቆማል … ሰው ወርዶ ተመልሶ ሲሳፈር ይሰማኛል ። ነገሮችን እየመዘንኩ ያለሁት በጆርዬ በማዳመጥ ብቻ ነው ።

ፀሀይዋ እየከረረች ስትመጣ ይታወቀኛል … . መኪናው ውስጥም ይሞቃል… . ለልብስ አልባው አካሌ ጥሩ ሆኖልኛል ። ግን ወዴት እይወሰዱኝ ይሆን ? ለምንስ ይህንን ያክል መጓዝ አስፈለገ ? ራቅ አድርገው ገድለውኝ ሊመለሱ ይሆን ? ……… . አቤት ሃዘኔ … .

ከ 6-8 ሰዓታት የተጓዝን ይመስለኛል … አሁን ያለነው በረሃማ አካባቢ መሆኑን በፀሃይዋ ግለት መገንዘብ ችያለሁ ።መኪናው ሙሉ ለሙሉ እንደቆመ ከረዥሙ መኪና ላይ ደጋግፈው አንድ በር ከፍተው አይኔ ላይ የታሰረውን ፈትተውልኝ ወደ ውስጥ ገባ አድርገው በሩን በጀርባዬ ላይ ጠረቀሙት።
አንድ አይነት የበር ጩኅት… .የገደል ማሚቶ ያጀበው ።

ገና ከአሁኑ ሆድ ባሰኝ …ሃዘኔ ጥልቅ ከመሆኑ በስተቀር ምንም የምቀይረው ነገር የለም … . ያው የተለመደውን አንድ ቦታ ቆሞ የመዋልና ማደሩን ኑሮዬን ተያያዝኩት ።

አሁንም ቀናቱ አንድ ሁለት እያሉ ያልፋሉ ። ለእኔ ምንም ለውጥ የለም ። የተዘጋ ቤት … . ጨለማ ክፍል ።

የላይኛው አካሌን መሸፈኛ አልቆ አልቆ አንገቴ እና ደረቴ ጋ ብቻ ትንሽ ብጣሽ ጨርቅ ከመትረፉ በስተቀር እርቃኔን ሆኛለሁ ። ከኋላዋ ብትን ብላ ተቀዳ ያለቀች እጅግ አጭር ቁምጣ … . በቃ ምንም የለኝም ። ምን አይነት ፍርድ ላይ እንዳለሁም መለየት የማይቻልበት … ..

ፀሎቴን አልቋረጥኩም … .. ወደ እግዚአብሄር እጮሃለሁ … .. ከአሁን በኋላ የሰውን ልጅ የሚያምን አንጀትም … ልብም አይኖረኝም ፣ ፍጡር ፍጡርን እንደዚህ አድርጎ ከነነፍሱ ቆፍሮ ሲቀብር ።

እያደር የልብ ህመሜ እየባሰብኝ በመምጣቱና ትንፋሼም እየተቆራረጠ በመቸገሬ ብዙውን ጊዜዬን ግድግዳውን ደገፍ ብዬ በመቀመጥ አሳልፈዋለሁ ። አካሌንስ በዚህ አይነት ልረዳው ሞከርኩ … . ጭንቅላቴን ግን አልቻኩም፤ የማይጓዝበት ርቀት የለም … . እሱ የሚያስበው የሚተክዝበት አያጣም ። ለነገሩ ጭለማ ውስጥ ዓይን ማየት ካልቻለና ጆሮ መስማት ካቃተው… . አእምሮ የድሮውን መከለሱ ያለ ነው ብዬ ደመደምኩ ።

የሰው ልጅ በቀላሉ ነፍሱ ትወጣለች ብሎ የሚያስብ ካለ ግን የተሳሳተ ግምት መሆኑን በእኔ ማረጋገጥ ይቻላል… በእርግጥም መሞት ከነበረብኝ እዚህ ጨለማ ክፍል ውስጥ መሞት ነበረብኝ … ማንም ይህንን ሁለት አመት መቋቋም አይችልም። የሰው ልጅ ግን ብርቱ ነው… .እግዚአብሄር ካቆየው ይቆያል ።

አሁን ሁለት አመት እየሞላኝ ነው ። ብዙ ነገሮች ከጭንቅላቴ ቀስ በቀስ እየተነኑ ወጥተዋል … . የውጪው አለም ፈፅሞ ሊጠፉብኝ ነው ።

አንድ ቀን እንዲሁ እንደወትሮው በሬ ተከፈተ … . አለፍ አልፍ እያለ የተፈፀመ በመሆኑ

EthioLion.Com

ብዙም አልተደነቅሁም፤ እንደተለመደው ባትሪ በእጃቸው የያዙ ሰዎች በሩ ላይ ቆመው ወደ ውጪ እንድወጣ ጠየቁኝ … . መልስ ሲያጡ ግን ቀርበውኝ ደጋግፈው አንሱኝና የሆነ ነገር በትግሪኛ ተነጋግረው ተመልሰው በሩን ዘግተውብኝ ተመለሱ ። በግምት ከአንድ ሰዓት ያክል ቆይታ በኋላ በሩ እንደገና ተከፈተና ወደ ውስጥ ገብተው እግሬ ላይ ያለውን ሰንሰለት ፈቱልኝ … . ቀና ብዬ ሰውዬውን ለማየት ሞከርኩ … ዙሪያዬ በእጃቸው የያዙት ባትሪ ከሚፈጥረው ብርሃን በስተቀረ ምንም ማየት አልቻልኩም ………… . የእግሬ ሰንሰለት በመፈታቱ እስከ ዛሬ ስደነግጥ ከነበረው በላይ ደነገጥኩ ፤ 'እንዴ ለምን' ? የሚል ቃል ሳላስበው ከአፌ ወጣ ፤ሳቅ ተሰማኝ … . የመገረም ሳቅ …። ለነገሩ እኔ እንኳ ለምን የእግሬን ሰንሰለት ትፈታላችሁ ለማለት አልነበረም … .. አንድ አንዴ ሊፈፀም አይችልም ብለን የወሰነው ነገር ተፈፅሞ ማየት ግራ ስለሚያጋባ እንጂ ። እግሬን ከፈቱልኝ በኋላ ተነስና ውጣ አሉኝ ። አንደኛ እግሬ መፈታቱ ሲገርመኝ ወዴት እንደሚወስዱኝ ደግሞ ፍርሃት ለቀቀብኝ ። መቼም እንደዚህ ሲያደርጉኝ ኖረው … ከአሁን በኋላ ወደ ሰው መቀላቀል ወይም መፈታት ይኖራል የሚል ነገር በውስጤ ከሞተ ዘመን የለውም ። ስለዚህ የዛሬዋ ዕለት እንኳ የመሞቺያዬ ናት ብዬ ደመደምኩ ።

እየተራመድኩ አብሪያቸው ወጣሁ … .. በባትሪ እየታገዝን አንድ ደረጃ ወደላይ ወጣን … ከዚያም ረዘም ያለ ኰሪደር በማለፍ አንድ ትልቅ በር ሲከፈት ወጋገን ታየኝ ። እንዴ ! ? … . አሁንም ተገረምኩ ። ወደውጪ መውጣት ሁሉ ፈራሁ … .

እምቢ ለማለት እየዳዳኝ … .. አንድ የተሳሳቱት ነገር መኖር አለበት እንጂ እያልኩ አሰብኩ ፤ የእጄ ሰንሰለት ግን እንዳለ ነው ። በሩን ሲከፍቱ አብረውኝ ሁለት ሰዎች አሉ ። ከወደ ውጪው ሌሎች መሳሪያ ያነገቱ ወታደሮች ቆመዋል ። የበሩን ደፍ እንደአለፍኩኝ በሁለት አመት ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰውነቴን ሙሉ ለሙሉ ማየት ቻልኩኝ … .. በጣም ያሳዝናል … እራቁቴን ነኝ ማለት ይቻላል ።

እግሬ ፣ እጄ … .. ሰውነቴ ሁሉ አመድ መስሏል ። ውጪውን ስቃኝ በረጃጅም ዛፎች የተሸፈነ አካባቢ ውስጥ ነኝ … . ወዲያው ግን አጅበውኝ ከቆሙት ወታደሮች መካከል አንደኛው ወደ አንድ አቅጣጫ ብቻ ማየት እንደሚፈቀድልኝ ቆጣ ብሎ ትዕዛዝ ሰጠኝ ። ቀጥሎም ከፊት ለፊቴ ወደ ቆመ አውቶብስ እንድገባ ነገርኝ … ወደ ውስጥ ገብቼ የተሰጠኝ ቦታ ላይ ቁጭ አልኩኝ … .. አንዲት ቀጭን ትዕዛዝ ወዲያው መጣች … .. ወደታች አጎንብሼ ወደ መኪናው ወለል ከማየት በስተቀር ቀና ብዬ ወደ ሌላ አቅጣጫ ብመለከት ከባድ ችግር እንደሚገጥመኝ ተነገረኝ ። ትዕዛዙን ተግባራዊ ከማድረግ ውጪ አማራጭ አልነበረኝም ። እየቆየ ግን ብዙ ሰዎች ( ወታደሮች ይመስሉኛል ) አውቶብሱን ሞሉት ።

በውስጤ ብዙ ነገሮች ተመላለሱ … .. ከዚህ ሁሉ የብቸኝነትና የእንግልት እስር ቆይታ በኋላ ለምን ዛሬ በድንገት ሰው ሁሉ እንዲያየኝ ፈቀዱ ?…… አልገባህ አለኝ ። ለበጐ ከሆነስ … . ለምን የእጄን ሰንሰለት አይፈቱልኝም ? መላቅጡ ጠፋኝ ።

መኪናው ተንቀሳቅሶ መንገድ ጀምረናል ። እኔም ወለሉን እያየሁ አሰላስላለሁ … . ረጅም መንገድ ነው … .አልፎ አልፎ መኪናው ይቆማል … .. ተመልሶም ጉዞውን ይቀጥላል … . ወደ ሌላ እስር ቤት ሊያዛውሩኝ ይሆን ? ………… ..የመኪናውን ወለል እያየሁ በጭንቀት እብሰለሰላለሁ ።

በግምት ከ 8 ሰዓት ጉዞ በኋላ ግን መኪናው ከተማ ውስጥ ይጓዝ ጀመር … በጭላንጭል ከማየው የመኪና መተላለፍና የምጓዝበት አውቶብስ ፍጥነት መቀነሱ … ከተማ ውስጥ እንዳለን ይነግረኛል ።
በመጨረሻ ግን ያለሁበት መኪና ሙሉ በሙሉ ቆመና ውስጥ ያሉት ወታደሮች እዚያው እንደተቀመጡ እንድነሳ ተነገረኝ ። በማጎንበስ ብዛት ድንዝዝ ያለኝን አንገቴን በትግል ወደላይ ቀና በማድረግ ብድግ ስል ተገረምኩ ። ያለሁት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ደብረ ዘይት መንገድ በቅሎ ቤት እየተባለ ከሚጠራው ሰፈር … ከአማልጋሜትድ ሊሚትድ ጐን አዲስ ከተሰራ ባለ ቢጫማ ቀለም የተቀባ ህንፃ ቅጥር ግቢ በወታደሮች ታጅቤ ገባሁ ። ሁለት እጄ አሁንም እንደታሰረ ነው ። እርቃኑን ያለው አካሌም አሸማቀቀኝ … . ጀንበር እያዘቀዘቀች ያለችበት የአዲስ አበባ አየር ቅዝቃዜ ተሰማኝ ።

ወዲያው ግን በሁለት ህንፃዎች መካከል ወደ አለች ክፍተት ውስጥ ተሸሽጌ እንድቆይ አንድ መሣሪያ ባነገተ ወታደር ትዕዛዝ ተሰጥኝ ። ወደ ህንፃዎቹ መካከል ገባሁ … . ቅዝቃዜውን ግን አልቻልኩትም ………… .

መሳሪያ ካነገተው ወታደር ጋር ተፋጠናል … .. አሁን ብርሃን ስለአየሁ ነው መሰለኝ በፍፁም ወደዚያ ጨለማ የስቃይ ጉሮኖ እንዲመልሰኝ እንደማልፈቅደለት ለእራሴ ቃል ገባሁ … .. ተኩሶ ይግደለኝ በቃ!

ወታደሩ አሁንም አፍጦ ያየኛል … . እርግጥኛ ነኝ እርቃኔን ያለው ሰውነቴ ግራ ሳያጋባው የቀረ አይመስለኝም ። በዚሁ ሁኔታ እያለሁ ሰዓታት ማለፍ ጀመሩ ። ‘ ዝም ብዬ ወደ ወታደሩ ልሩጥና ተኩሶ ይምታኝ ? ወይስ ወደ ኋላዬ ልሩጥ ? ብቻ መሮጥ እንዳለብኝ ወሰኛለሁ … .. የመጨረሻዋን ውሳኔ ለማድረግ ስዘጋጅ የሆነ ሰው በትግሪኛ ወታደሩን ሲያናግረው ሰማሁ ። ወዲያውኑ ወታደሩ ምልክት ሰጥቶኝ ከተሸሸኩበት ስወጣ አንድ ግዙፍ ጠይም ባለ ሻለቃ ማዕረግ ጐልማሳ ወደ እሱ እንድንቀርብ በአማርኛ እያናገረኝ በመገረም አይነት የእጄ ሰንሰለት እንዲፈታልኝና የሆነ ልብስም እንዲያመጡልኝ ይናገራል ።ወዲያው የእጄ ሰንሰለት እንደ እግሬ ሁሉ በሁለት አመቱ ነፃ ሆነ ።አንዲያውም ሸሚዝና ሱሪም አምጥተውልኝ ለበስኩ ።

የማየውን ማመን አቃተኝ … .. ግዙፉ ሰውዬም ‘ ሻለቃ በሪሁ እባላለሁ ‘ ብሎ እራሱን አስተዋወቀኝ ።ቀጥሎም ወደ ወታደሩ ዞሮ “ ያንንም ወደዚህ አምጡት “ አለው ።ግራ ገባኝ … . ማንን ይሆን …… ?

ወታደሩ ሲመለስ ግን ቀጠን ረዘም ያለውን ዓይነ ትልልቁን ጠይም የሥራ ባልደረባዬንና ጥሩ ቅርርብ ያለንን ሰው ይዞ መጣ ።ዳንኤል በየነ ነው ። ምን እየተካሄደ እንዳለና ይህንን የስራ ባልደረባዬን እዚህ ሊያመጣው የቻለውን ጉዳይ መገመት ተሳነኝ ።

ጓደኛዬ ቀጠን ብሎ ፊቱ በፀጉር ( ፂም ) ተሸፍኗል ። ፀሀይ ያልነካው አይነት ሆኖ ጠይም ፊቱ እንደመቅላት ፈካ ያለ ይመስለኛል … .. አንድ ነገር ግን በልቤ ጠረጠርኩ … . ያሳሰረኝ ይሄ የቅርብ ወዳጄና የስራ ባልደረባዬ ይሆን ? አሁንስ ይዘውት የመጡት እንዲመሰክርብኝ ይሆን ? ከእራሴ ጋር ተሟገትኩ ። ሊሆን አይችልም ። ይህንን ወዳጄን ደህና አድርጌ አውቀዋለሁ … .

ወደ እኔ እየተጠጋ ሲመጣና አይን ለአይን ግጥም ስንል … በመገረም እጄን አፉ ላይ አድርጌ አፉን ከፍቶ ተመለከተኝ … .. ዘለግ ያሉት ቀጫጭን ጠይም ጣቶቹ ሙሉ ለሙሉ አፉን ሊሸፍኑለት አልቻሉም … . ክፉኛ መደንገጡ ያስታውቅበታል ። እርግጠኛ ነኝ የሚያየውን ማመን አቅቶታል ።
እኔም ዝም ብዬ አየዋለሁ ። የሁለታችንንም ዝም ብሎ ተፋጦ መተያየት የተመለከተው ሻለቃ በሪሁ የሆነ ጥያቄ ይጠይቃል ። ያስተዋለው ስለሌለ እንደገና ይጥይቀናል … " አትተዋወቁም እንዴ " ? ነበር የሻለቃ በሪሁ ጥያቄ ። እኔም ሆንኩ ጓደኛዬ ለሻለቃው ጥያቄ መልስ ማግኘት የቻልን አይመስልም … . በመካከላችን ዝምታ ነገሰ በየራሳችን ጥርጣሬ የተጠመድን ይመስላል …… ..
ሻለቃው ለሶስተኛ ጊዜ ያንኑ ጥያቄ ሲጠይቀኝ ግን እኔ ሊሆን ይችላል ብዬ ልቤ የጠረጠረውን " እንዲመሰክርብኝ ከሆነ ያመጣችሁት… . የሚለውን ለመስማት ዝግጁ ነኝ ……… ..
አልኩት ። የስራ ባልደረባዬ የሃዘንና የትዝብት ፈገግታ ሲያሳየኝ ጥርጣሬዬ ከንቱ እንደነበረ በዚያችው ቅፅበት ተረዳሁ ።
ሻለቃው ግን ረጅም ትንፋሽ አውጥቶ … . እዝያው የህንፃው ውህ ልክ ላይ እኔንና የስራ ባልደረባዬን ግራና ቀኝ በማድረግ መሃከላችን በመቀመጥ " ኢትዮጵያ ትፈልጋቹሃለች" በሚል ንግግር ማድረግ ጀመረ ……… ..

ኢትዮጵያ ትፈልጋቹኋለች ……… . ምን ማለቱ ይሆን ? እላለሁ በልቤ ።ቀጥሎም በተወነጀላችሁበት ጉዳይ አንዳችም ማስረጃ ማግኘት አልቻልንም … .. ስለዚህ ወደ ክፍላችሁ ተመልሳችሁ ተከራከሩ አለን ።
ከውስጤ አንድ ነገር ለቆኝ ሲሄድ ይሰማኛል … .. በህመም ድቅቅ ያለው ሰውነቴ በአንድ ገዜ ጤንነት ሲሰማው ይታወቀኛል ። በተስፋ ማጣት የተሰበረው መንፈሴና እየሞተ ያለው አካሌ ሲጠነክርና ሰለመልም ። ሻለቃው ቀጥሎም እናንተ የሀገር ሃብት ናችሁ …… .. ኢትዮጵያን አደራ … .. እያለ ብዙ ብዙ ይናገራል ።
የመጀመሪያውን እንጂ ሌላውን ዲስኩር አልሰማሁም ። የመቃብሬ ድንጋይ የተፈነቀለልኝ ያህል ነው የሆነብኝ ።

ከመጀመሪያዋ ዕለት ጀምሮ የደረሰብኝ በደል በጭንቅላቴ ይመላለሳል ። ሁለት አመት ሙሉ የሰውን ልጅ እጅና እግሩን በሰንሰለት አስረው ከምድር በታች በተቆፈረ ጨለማ ክፍል ውስጥ ጥለው ሲያበቁና አምላክ በምህረቱና በቸርነቱ ባቆያት ነፍስ ዛሬ ተመልሰው የእነሱኑ የስልጣን ዘመን ለማራዘም ዘይደው "ኢትዮጵያ ትፈልጋቹሃለች" የሚለውን አነጋገር ነው እየደጋገምኩ የማውጠነጥነው: :

ኢትዮጵያ የትም ተጥሎ ነፍሱ ያልወጣች እሬሳ ለምን ይሆን የምትፈልገው ? እንቆቅልሽ ነው የሆነብኝ።

ጭልጥ ብዬ መሄዴን ያስተዋለው ሻለቃ ትከሻዬን በእጁ መታ አደረገና አነቃኝ ። የመዝለል ያክል በርግጌ ከሩቅ ጉዞዬ ተመለስኩ ።ሻለቃው ግን አሁንም ይደሰኩራል ……… . እዚህ በእስር ቆይታችሁ ውስጥ ያጋጥማችሁን ለማንም እንዳትናገሩ ቃል መግባት አለባችሁ …… . ይህንን ጉዳይ ከእናንተ በስተቀር የሚያውቅ የለምና ከሌሎች ሰዎች ቢሰማ የነበራችሁበትን ታውቃላችሁና ወደዚያው ነው የምትመለሱት … ስለዚህ አፋችሁን ሰብስቡ አለን ።
መስማማታችንንም አንገት በመነቅነቅ አሳየነው ። … ማን ወደዚያች መቃብር ይመለሳል ።

መስማማታችንን ያየው ሻለቃም “እንግዲያውስ ከተግባባን ፅሁፉ ተዘጋጅቷልና እዚህ ላይ ትፈርማላችሁ” ብሎ በኮምፒዩተር የተፃፈ ወረቀት አወጣና ለሁለታችንም ሰጠን ። ማየትና ማንበብ በፍፁም አልፈለኩም ። እኔ በበኩሌ ከዚህ ትወጣለህ የሚለውን ልስማ እንጂ ያሉኝን ቢሉኝ ለመፈራረም ዝግጁ ነኝ ።ወረቀቱን እንደተቀበልኩ ተጣድፌ በትልቁ ፊርማዬን አሰፈርኩ ። ሻለቃውም ሁኔታዬን አይቶ ነው መሰለኝ “አነበብከው” ብሎ ጠየቀኝ ፤ ከአንተ የሰማሁትን ተስማምቼበታለሁና ችግር የለውም አልኩት ።

ሻለቃው ትሁት ለመሆን ሞክሯል …… ያለ ምንም ወንጀል ያንን ያክል ፍዳና መከራ መቀበበላችን ያሳዘነው ይመስላል ። ደጋግሞ ግን “እናንተ እኮ የሀገር ሃብት ናችሁ” ይለናል ። “ሬሳ አሁን እንዴት ሃብት ሊሆን ይችላል” ?…… . እላለሁ በውስጤ ።

ሻለቃው በመቀጠልም አሁን መኪና አዝላችሁና ወደ ክፍላችሁ ወደ ደብረ ዘይት ያደርሷችኋል … .. በማለት ወደ አንዲት ዋዝ ወታደራዊ መኪና አመልክቶን ከሾፌሩ እና አንድ አጃቢ ጋር አገናኘን ።

ሳላስበው እምባዬ በፊቴ ላይ ፈሰሰ … .. በምንም ተዓምር ይሂ ቀን ይመጣል ብዬ አላሰብኩም … .. ሌላው ቀርቶ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት እንኳ እሮጬ አምልጬ ተኩሰው ይምቱኝ (ይግደሉኝ ) እያልኩ የምመኝ ሰው አሁን ወደ ደብረ ዘይት ሂዱ መባልን ስሰማ ደስታም ፣ ሃዘንም ፣ ቅስም መሰበርም ተባብረው እምባዬን መቆጣጠር እንዳልችል አደረጉኝ ። ሻለቃውም ስሜን ጠርቶ “አይዞህ … .. እናንተ እኮ ነፃ ሰዎች ናችሁ እመነኝ” አለኝ ።

“ነፃ ናችሁ” የሚለውን ቃል እግዚአብሄር ከሰማይ ወርዶ የሚያናገርኝ ያክል ነው የተሰማኝ ። ሆደ ባሻ ሆኛለሁና የባሰውን እምባዬን መቆጣጠር አቃተኝ ። ሻለቃውም መልካም ዕድል ተመኝቶልንና የኢትዮጵያን ነገር አደራ ብሎን ሲለየን እኛም ወደ መኪናዋ ገባን ።

መኪናዋ ውስጥ ሾፌሩ ፣ ከጐኑ ደግሞ አንድ የመኰንንነት ማዕረግ ያጠለቀ ሰው …… ከኋላም እኔ በስተቀኝ ጓደኛዬ ዳንኤል ደግሞ በስተግራ ተቀምጠናል ።

ሾፌሩና ከጐኑ የተቀመጠው መኮንን ሃሳባቸው ወደ እኛ አይመስልም … .. የጦፈ ጨዋታ በትግሪኛ ቋንቋ ይዘዋል ።እየተጯጯሁ ይስቃሉ … . አንዴም ወደ እኛ አቅጣጫ ዞር ብለው አላዩም ።

እኔና ጓደኛዬ ዳንኤል አንዲት ቃል አንተነፍስም … .. ጐን ለጐን እንቀመጥ እንጂ ሰውነታችን እንኳ እንዳይነካካ ወደ እየራሳችን ጥግ ተስበን ነው የተቀመጥነው ። ትንፋሻችን እንኳ አይሰማም ።

እኔ በይበልጥ አንድ ጊዜም ወደ እሱ ዞሬ አላየሁም … . ወደ ቀኝ ትከሻዬ በኩል ዞሬ ውጪ ውጪውን አያለሁ ። አይኔ የሚያይ ይምሰል እንጂ እየተፈጠረ ባለው ሁኔታ ዝብርቅርቅ ብሎብኝ ሃሳቤን መሰብሰብና በቅጡ ማሰብ ተስኖኛል ። ጓደኛዬም እኔን የማናገር ሃሳቡም ያለው አይመስልም … . እጅግ ማዘኑን ፣ ልቡ መሰበሩንና ተስፋ መቁረጡን ገና ቅድም እንዳየሁት ከፊቱ አንብቤያለሁ ።

EthioLion.com

ዳንኤል በየነ ደብረ ዘይት ከተማ ተወልዶ ያደገ ነው ። አባቱም በአየር ሀይል መስሪያ ቤት ወስጥ ባለ ከፍተኛ ማዕረግ ባለቤትና ለረዥም ጊዜ አገልግለው በጡረታ በክብር ከመስሪያ ቤቱ የተሰናበቱ የአየር ሀይሉ ዕንቁ ልጅ ናቸው ። ጓደኛዬም የአባቱን ፈለግ ተከትሎ አየር ሀይል በበራሪነት ሙያ ተቀጥሮ በውጪ አገርና በአገር ውስጥ የሚሰጠውን የበረራ ስልጠና በከፍተኛ ማዕረግ በመመረቅ እነሆ ዛሬ በጀት ማሰልጠኛ ስኳድሮን በአስተማሪነትና በተዋጊ ስኳድሮንም በተዋጊ በራሪነት አገሩን በቅንነት እያገለገለ የነበረ ከፍተኛ ተስፋ የሚጣልበት የሀገር ሀብት ነበር ።

ተጫዋችነት መሽቀርቀርና የማህበራዊ ኑሮ ግኑኝነትን ማሳመርና ማጣፈጥ ከሁሉም በላይ ደግሞ ሰው አክባሪነትና ደግነት በሙያውም እንከን የማይወጣለት ጉበዝናና ታታሪነት ዋነኛ መለያዎቹ ናቸው ።
በይበልጥ በስራ ተወጥሮ ለከረመ አካልና አእምሮ መድሃኒት ነው ፡ የስራ ባልደረቦቹንም ይሁን ጓደኞቹን አሰባስቦ ዘና የሚያስደርግ ሁኔታውችን መፍጠር የተካነበት ነው ። የመደሰት እንጂ የመጨነቅ ሰው አይደለም ፤ ዛሬ ግን እዚሁ አጠገቤ ተቀምጦ ትክዝ ብሎ በራሱ ዓለም ውስጥ ገብቶ እኔን ለማናገር እንኳ አንጀት አጥቷል ።

መኪናዋ ገጠር መሰል የአዲስ አበባ - ደብረ ዘይትን መንገድ ይዛ ትሽመጥጣለች … . ከሁለት አመት በፊት የማውቃቸው ገጠራማ የመሬት አቀማመጦችን አሁንም አሁንም እየደረስንባቸው አያቸዋለሁ ።

ዱከም ስንደርስ ለአይን ያዝ ማድረግ ጀምሯል ። ዱከም ግን ተቀየረችብኝ … ያደገች ትመስላለች … የምሽት መብራቶቿ ደመቅ ብለዋል … .. የየቤቶቹ የግድግዳ ቀለማት ሁሉ ተቀይረው ታዩኝ ። ዱከምን አለፍ እንዳልን ግን ከሁለት አመት በፊት የታፈንኩባትን ቦታ ቀድሜ ለማግኘት በሾፌሩ በኩል አሻግሬ ማየት ጀመርኩኝ ። አካባቢውን ሁሉ እቃኛለሁ … . መጨላለም ጀምሯልና እድለኛ አልሆንኩም ። ቦታዋን ድንገት አልፈናታል ።

ወደ ደብረ ዘይት እየተጠጋን ስንሄድ ግን የልቤ ምት እየፈጠነ መጣ ። ይህቺን ከተማ ጥርሴን ነቅዬባታለሁ … እያንዳንዱን መንደር አውቃታለሁ ፤ ክፉም ደግም ትውስታዎች አሉኝ ። ልቤ ሽብር ሽብር ይልብኝ ጀመር … . የእናቴ ጉዳይ የልብ ቁስል ሆኖ ለሁለት ዓመታት አሰቃይቶኛል … .. በሰላም አገኛት ይሆን ? ብቻ በእኔ ምክንያት አንድ ነገር ባልሆነች ።

የዛሬ ሁለት ዓመት እናቴን ከመለየቴ በፊት ለአንድ አመት ያክል በልብ ህመም ምክንያት በህክምና ስትረዳ ነው የቆየችው ። ሀኪሞቿም ከፍተኛ ጥንቃቄ እንድታደርግና ከማንኛውም ጭንቀትና ከባድ ስራ እራሷን እንድትጠብቅ ከማንስጠንቀቂያ ጭምር ነግረዋት ፣ የሚቀራትንም ዘመን ያለማቋረጥ ሶስት አይነት መድሃኒት እየወሰደች እንደምትኖር ፣ መድሃኒት መውሰዱን ለአንዲት ቀን እንኳ ብታቋርጥ ህይወቷ አደጋ ላይ እንደሚወድቅ አሳውቀዋት እንደነበር ሁኔታው ሁሉ ፊቴ ላይ እየተደቀነ ይረብሸኝ ጀመር ።ወደ ደበረ ዘይት እየተጠጋን መምጣጣችንንም ጠላሁት ። እናቴን በህይወት የማግኘቱ ጉዳይ እጅግ አጠራጠርኝ ። እኔ የደረስኩበትን ሳታውቅ በሰላም ትኖራለች ማለት ዘበት ነው (ይህንን ሁሉም እናቶች ያውቁታል ) … .. ሰላም ከሌላት ደግሞ ህይወቷ አደጋ ላይ ይሆናል … ጭንቀትንና ስቃይን መቋቋም እንደማትችል በሃኪም የተመሰከረላት ነፍሷ ደግሞ ይህንን መከራ እንደማትቋቋመው ታወቀኝ ።

ከጐኔ የተቀመጠው ጓደኛዬ ዳንኤል ወደ ደብረ ዘይት ከተማ እየገባን ስንመጣ አልፎ አልፎ ወደ እኔ ይመለከት ጀመር ። እሱ ግን ከእኔ የተሻለ የተረጋጋ መንፈስ ያለው ይመስለኛል …… . ለመነጋገር ግን አልደፈርንም ። ሁለት አመት ሙሉ ሰው ማናገር አይደለም ማንንም በዓይኔ እንኳ እንዳላይ ይደረግብኝ የነበረው ነገር በደቂቃ ከውስጤ ሊወጣ አልቻለም ። ዳንኤልም ቢሆን ከእዚህ የተለይ አይሆንም ።

መኪናዋ የደብረ ዘይትን ከተማ መሃል ለመሃል እየሰነጠቀች አልፋ ከከተማዋ ምስራቅ ጫፍ ናዝሬት መንገድ በስተቀኝ ጠርዝ ላይ ከሚገኘው የኢትዮጵያ አየር ሀይል ዋና መምሪያ በር ላይ ሄዳ ቆመች ።

ዋናው በር ታድሶ በጥሩ ሁኔታ ተሰርቷል … . በውሃ ሰማያዊ መደብ ላይ “የኢትዮጵያ አየር ሀይል” የሚል ፅሁፍ በወርቃማ ቀለም በትላልቁ ተፅፏል ። ከፅሁፉ አናት ላይ ክቡ “አረንጓዴ ፣ ቢጫ ፣ ቀይ” ኤምብለም የኢትዮጵያ አየር ሃይል አርማ ተነስቶ በሌላ ዘምባባ መሰል የፖለቲካ ፓርቲ አርማ ስዕል ተቀይሯል ። ብዙም አልገረመኝም ። እነኚህ ሰዎች ጉልበተኛ ተቆጪ ያጡና እንዳሻቸው አዳሪ መሆናቸውን ከበቂ በላይ አይቻለሁ ።

እነዚህን ሁኔታዎች እያስተዋልኩ ባለሁበት ቅፅበት አንድ መሳሪያ ያነገተ ወታደር ከሹፌሩ ጐን ከተቀመጠው ባለ መኮንን ማዕረግ አጃቢያችን ጋራ ለአጭር ጊዜ ተነጋግረው ወደ ውስጥ እንድንገባ ፈቀደልን ።

በዚህ በር በኩል ስወጣና ስገባ በዚያን ወቅት ከነበርኝ እድሜ አንፃር ሳስበው ከግማሽ በላይ እድሜዬን አሳልፌያለሁ ።

ለድሮ የአየር ሀይል ግቢ የግርማ ሞገስ ድባብ ነበረው … .. ለብዙዎቻችን የአየር ሀይል ባልደረቦች መስሪያ ቤቱ የእናትና የአባት ያክል ነው ። አሳድጐናል ፣ አስተምሮናል ፣ ክፉና ደግን ለይተንበታል ። መስሪያ ቤቱ የግል ቤታችን ያክል ነው ። ሲከፋንም ሲደላንም አየር ሀይል ሁልጊዜ አብሮን አለ ። ሰራዊቱ እንደወንድማማች ይቀራረባል ፤ አብሮ ይበላል … . አብሮ ይጠጣል ። አለቆቻችን ወይ እንደ አባት አለበለዚያም እንደ ታላቅ ወንድም ናቸው ። ስናጠፋ ይቆጣሉ … ካበዛነውም ቅጣታቸው የዋዛ አይደለም ። እርዳታቸውን ስንፈልግ ግን ከጐናችን ናቸው ። ያንፁናል ያስተካክሉናል ። በመስሪያ በቱ እንድንኮራና እንድንመካ አደርጉናል ።

እኔ በሃሳብ ወደ ኋላ ጭልጥ ብዬ ልሂድ እንጂ የያዘችን ሩስያ ሰራሽ ዋዝ ወታደራዊ መኪና ዋናውን በር አልፋ ወደ ውስጥ እየገባች ነው ።

ለድሮ አሁን እየሄድንበት ባለነው መንገድ ግራና ቀኝ ጥቅጥቅ ያለ የባህር ዛፍ ተክል ነበር ። ይህ ዛፍ ነበር እንግዲህ የግቢው ድባብና ሞገስ … .. አሁን ግን በደበዘዘው ምሽት ሳየው ዛፉ የተቆረጠበት ግማሽ አካሉ (ጉቶ ) በዛብኝ ።

ጥቅጥቅ ያለውም ዛፍ ከመሳሳቱ የተነሳ በአሻገር ያለውን ሜዳና ህንፃ ማየት ቻልኩ … .. ለነገሩ ዘመነኞቹ ባለስልጣኖች እንደ ገቡ ሰሞን ያለርህራሄ ዛፉን ሲቆራርጡ እያየሁ አንጀቴ ድብን ይል ነበር ።ዛሬ ዛሬ ግን የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ሌባ ሌባ … .. እያሉ መጣራታቸው መልስ እንዳገኝ አድርጐኛል።

EthioLion.com